# የንግድ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

## (የስልጠና ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# የንግድ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

# (የሥልጣና ሞጁል)

ህዳር 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

# የንግድ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

አዘጋጆች፡-

ዶ/ር መኮነን ቦጋለ (ጂማ ዩኒቨርስቲ)

ዶ/ር አወቀ አሸናፊ (የኢትዮጲያ ሲቪል ሰርቪሲ ዩኒቨርስቲ)

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኁላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ዲዛይን፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ

© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

ህዳር 2017 ዓ.ም

# ማውጫ

ማውጫ ..... 1
መግቢያ ..... 3
የሞጁሉ አጭር መግለጫ ..... 3
የስልጠናዉ ዋና ዓላማ፤ ..... 3
የስልጠናዉ ዝርዝር ዓላማዎች፤ ..... 3
የስልጠናው ተሳታፊዎች፤ ..... 4
ለስልጠናው የተመደበው ጊዜ፤ ..... 4
የማሰልጠኛ ዘዴዎች፣ ..... 4
መርጃ መሳሪያዎች፤ ..... 4
የሞጁሉ አወቃቀር፤ ..... 5
ምዕራፍ አንድ ..... 6
የሙስና ወንጀል ምንነት ..... 6
1.1 መግቢያ ..... 6
1.2 የምዕራፉ ዓላማ ..... 6
1.3 የተፈቀደው ጊዜ፤ ..... 6
1.4 የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤ ..... 6
1.5 የሙስና ወንጀል ምንነት ..... 6
1.6 የሙስና ዓይነቶች ..... 8
1.7 የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት ..... 10
1.8 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ..... 12
የምዕራፉ ማጠቃለያ ..... 23
የማጠቃለያ ጥያቄዎች ..... 23
ምዕራፍ ሁለት ..... 26
የንግድ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት ..... 26
2.1 መግቢያ፣ ..... 26
2.2 የምዕራፉ ዓላማ፤ ..... 26
2.3 የተፈቀደው ጊዜ፤ ..... 26
2.4 ስለ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አጭር ማብራሪያ ..... 26
2.5 የማነቃቂያ ጥያቄ ..... 27
2.6 የንግዱ ዘርፉ የሙስና ተጋላጭነት ..... 28
የምዕራፉ ማጠቃለያ ..... 30

የማጠቃለያ ጥያቄዎች 30
ምዕራፍ ሶስት 32
ሙስና በንግድ ዘርፍ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት እና የመከላከያ ስልቶች 32
3.1 መግቢያ፤ 32
3.2 የምዕራፉ ዓላማዎች፤ 32
3.3 የተፈቀደው ጊዜ፤ 33
3.4 የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤ 33
3.5 ሙስና በንግዱ ዘርፍ የሚያስክትለው ተፅዕኖ/ጉዳት 33
3.6 የሙስና መከላከያ ዘዴዎች፡ 36
የምዕራፉ ማጠቃለያ 49
የማጠቃለያ ጥያቄዎች 49
የሞጁሉ ማጠቃለያ 52

# መግቢያ

## የሞጁሉ አጭር መግለጫ

ሙስና በአንድ ሀገር በሁሉም ዘርፎች ውስጥ በመከሰት በሀገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ በማስከተል ሀገር እንደሀገር በማይቀጥልበት ደረጃ ማድረስ የሚያስችል ወይም ተቋማትን የማፍረስ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ተለዋዋጭነት ባህሪ ያለው አደገኛ የሆነ የወንጀል አይነት ነው፡፡ ኢትዮጵያም በዚህ ወንጀል ከተጎዱ ሀገራት አንዷ በመሆኗ የፌደራል የስነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ይህንን ብልሹ አሰራር ለመቀነስ የስራ ዘርፍን ያማከለ ስልጠና በመስጠት ሙስናን መቀነስ እንደ አንድ ስትራቴጂክ ግብ በማቀድ እየሰራበት ይገኛል፡፡ ይህ የማሰልጠኛ ሞጁልም የተዘጋጀው በኢትዩጵያ የንግዱን ዘርፍ ትኩረት በማድረግ በዘርፉ የስራ ክንውን ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ልዩ ልዩ የሙስና ዓይነቶችን፣ ተጋላጭ ሁኔታዎችን፣ ሙስና በኢኮኖሚና በማህበራዊ መስተጋብር ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖዎችና መከላከያ ስልቶችን በማካተት ለዘርፉ ሰራተኞች ተጨባጭ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው፤ ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ፤ እንዲሁም አመለካከታቸውን እንዲያሻሽሉ በማድረግ በሀገራችን እና በተቋማት የሚከሰተውን ሙስናን በብቃት እንዲከላከሉ ለማድረግ ነው፡፡

ሞጁሉ በአጠቃላይ ሦስት ምዕራፎች ሲኖሩት፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ የሙስና ፅንሰ-ሀሳብ እና የሙስና ዓይነቶች በዝርዝር ይቀርባል፡፡ በምዕራፍ ሁለት የንግድ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነትን በተመለከተ ተብራርቷል፡፡ ምዕራፍ ሶስት ሙስና በንግዱ ዘርፍ ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖን እና የሙስና መከላከያ ስልቶች በሰፊው ቀርቧል፡፡

## የስልጠናዉ ዋና ዓላማ፤

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና በስሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት ሰራተኞች በዘርፉ የሚስተዋለውን ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን እንዲከላከሉ ለማስቻል ነው፡፡

## የስልጠናዉ ዝርዝር ዓላማዎች፤

በዚህ ስልጠና መጨረሻ ሰልጣኞች የሚከተሉትን ፅንሰ-ሀሳቦች በመገንዘብ ክህሎታቸውን እና አመለካከታቸውን በማሻሻል በስራ ቦታቸው መተግበር ይችላሉ፡፡

- የሙስናን ምንነት እንደ አጠቃላይና በተለይም ከንግዱ ዘርፍ አንፃር ይረዳሉ፡፡

- በኢትዮጵያ ንግድ ዘርፍ አሰራር ሂደት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የተለያዩ የሙስና ዓይነቶችና ብልሹ አሰራሮች ይለያሉ፤ ገለጻ ያደርጋሉ፡፡
- በንግዱ ዘርፍ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነቶች ይለያሉ፤ ትንታኔ ይሰጣሉ፡፡
- ሙስና በንግዱ ዘርፍ የልማት አጀንዳዎች ላይ የሚያደርሰውን ጉልህ ተፅዕኖ ይረዳሉ፡፡
- የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የመከላከያ ስልቶችን በመለየት አተገባበራቸውን ያውቃሉ፡፡
- የሙስና መከላከያ ስልቶች እና እርምጃዎች ውጤታማነት ይገመግማሉ፡፡

## የስልጠናው ተሳታፊዎች፤

- የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና በስሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት አመራሮች እና ሰራተኞች ናቸው፡፡

## ለስልጠናው የተመደበው ጊዜ፤

- ስልጠናው የ 2 ቀናት (12 ስዓት) ስልጠና ነው፡፡

## የማስልጠኛ ዘዴዎች፣

- ቅድመ-ስልጠና ግምገማ
- የአምዕሮ ጎዳ ማንኮኮት (Brainstorming session)
- የገፅ-ለገፅ ገለጻ
- የማነቃቂያ ጥያቄዎች ማቅረብ እና መወያየት
- የመወያያ ጥያቄዎች ማቅረብ እና መወያየት
- ኬዞች ላይ ሰልጣኞች በቡድን እንዲወያዩ እና ሪፖርት እንዲቀርቡ ማድረግ፤
- ሮል ፕለይግ
- የልምድ ልውውጥ ማድረግ
- ድህረ-ስልጠና ግምገማ (ፈተና)

## መርጃ መሳሪያዎች፤

- የስልጠና ሞጁል
- የኤፌድሪ ስነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ስለ ሙስና እና ብልሹ አሰራር በተቋማት ላይ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት ውጤት ዶክመንት
- በንግዱ ዘርፍ የተከሰቱ የተለያዩ ከሙስና ጋር የተያዙ ኬዞች

- ስለ ሙስና የተጻፉ ተዛማጅ መጽሃፍት
- ላፕ ቶፕ
- ኤልሲዲ/ፕሮጅክተር
- ማርከር
- ፊሊፕ ቻርት

## የሞጁሉ አወቃቀር፤

የሞጁሉ በአጠቃላይ ሦስት ምዕራፎችን ያካተተ ሲሆን እነዚህም፡-

- **ምዕራፍ አንድ፡** የሙስና ወንጀል ምንነት እና የሙስና አይነቶች
- **ምዕረፍ ሁለት፡** የንግድ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት
- **ምዕራፍ ሦስት፡** ሙስና በንግድ ዘርፍ የሚያስከትለው ተፅዕኖ እና የሙስና መከላከያ ስልቶች

## ምዕራፍ አንድ

## የሙስና ወንጀል ምንነት

### 1.1 መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀብል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው፡፡ ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ይህ ምእራፍ የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎችን የሚቀርቡበት ምዕራፍ ነው፡፡

### 1.2 የምዕራፉ ዓላማ

ከዚህ ምዕራፍ ስልጠና በኂላ ሰልጣኞች፡-

- የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፤
- በሀገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፤

### 1.3 የተፈቀደው ጊዜ፤

- ይህን ምዕራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 4:00 ሰዓት ነው፡፡

### 1.4 የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤

1. ከጉቦ ውጭ የምታውቁትን የሙስና ወንጀል ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ፡፡

### 1.5 የሙስና ወንጀል ምንነት

ሙስና የእንግሊዝኛውን "Corruption" የሚለውን ቃል እንዲገለጽ የምንጠቀምበት ከግእዝ የተወሰደ ቃል ነው፡፡ ለሙስና ወጥ የሆነ ትርጉም ለመሰጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም

የተባበሩት መንግሰታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ህብረት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአውሮፓ ህብረት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን፤ የኢትዮጵያ የሙስና ወንጀልች ህግ እና የፀረ-ሙስና ህጎችን ብንመረምር ለሙስና ትርጉም ከመሰጠት ይልቅ የሙስና ወንጀሎች የሚባሉትን መዘርዘር ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡

ከዚህ አኳያ የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፤

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣ በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣ በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣ በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል“ የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል፣ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ “*... የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል...*” በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች፣ በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

የ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀለ ሕግ ሲወጣ የቀድሞዉን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በግልጽ ሽሯል፡፡ የ1996ቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ እንዲወጣ ምክንያት ከነበሩት ወንጀሎች መካከል ዋነኞቹ የሙስና ወንጀሎች እንደነበሩ በወንጀል ሕጉ ዉስጥ

ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅቶች ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሰራተኞች፣ በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡

## 1.6 የሙስና ዓይነቶች

የሙስና መገለጫው ብዙ አይነት ሲሆን ከትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ዝርፊያና ምዝበራ እንዲሁም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስልጣንን አላግባብ መገልገል ሊሆን ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ሙስና ዝቅተኛ (petty corruption)፣ ከፍተኛ (grand corruption) እና ስርዓታዊ ሙስና (state capture) ተብሎ ይከፈላል፡፡

### 1.6.1 ዝቅተኛ ሙስና (petty corruption)

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው፡፡ ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው፡፡

በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው፡፡ መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ ማደስ፣ የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግዢ፣ በተሽከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው፡፡

### 1.6.2 ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption)

ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስሌት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ትልልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት የሙስና አይነት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተሻሻለው የፌደራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/1997 "ከባድ የሙስና ወንጀል" ማለት፤

ሀ) ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀል ወይም

ለ) የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም

ሐ) በአገር ሉአላዊነት፤ ኢኮኖሚ፤ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰብ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ ወይም የሚችሉ የሙስናንጀሎች ናቸው በሚል ይደነግጋል፡፡

### 1.6.3 ስርዓታዊ ሙስና (systemic corruption)

የሀገሪቱን አጠቃላይ የመንግስት ስርዓት መዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፊያና ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሆነው ለማጥቃት የሚጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ሲስተሚክ ሙስና ህግ አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዲሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፊያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል፡ ፡ ከፍተኛ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic capture) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) ሊሆን የሚችል ነው፡፡

### 1.6.4 ፖለቲካዊ ሙስና (political corruption)

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች መንገድ መወሰንን ወይም እንዲወሰኑ ማድረግንና የአንድን ማህበረሰብ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሴቶችንና ልማዶችን የመጣስ ማንኛውንም ተግባር የሚመለከት ነው፡፡

ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Corruption)፣ የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በየተቋሙ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እንደየተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተልዕኮ የሚለያዩ ናቸው፡፡

## 1.7 የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች የተለየና ዉስብስብ የሆነ ወንጀል፡፡ የዚህን ወንጀል ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያድርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር፣ ለማጋለጥ ለመክሰስና አጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያድርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ፡፡ የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፤

### 1.7.1 የወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት

የሙስና ወንጀል በስሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጢር፣ በስምምነት፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያትም መፈፀሙን ለማወቅ የሚያችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አዳጋች ነዉ፡፡ የሙስና ወንጀሎች በአብዛኛዉ የሚፈጸሙት በዘርፉ እዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን አጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል ማስረጃ የማጥፋት አቅም ስላዉ ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል፡፡

### 1.7.2 የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት

የሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን በማስገኘትና በማካበት፣ የማይገባ መብትን በመስጠት፣ ሌሎችን የሚገባቸዉን ሀብት በማጉደል ወይም መብታቸዉ ላይ በደል በማድረስ በዋናነት ፍትሀዊነት መጓደልን ያስከትላል፡፡ ለአንዱ ያለግባብ ፍቃድ ወይም መብት በመስጠት ሌሎችን በመንፈግ በዜጎች እና በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባዉን እኩልነት ያጠፋል፡፡ ከዚህ ባለፈም በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባ ማህበራዊ ፍትህ ወይም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ያጠፋል፡፡ ዜጎችና

እና ልማት የሚገባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገባቸዉን መሠረታዊ አገልግሎት በጊዜና በጥራት እንዳይደረሳቸዉ ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ የሙስና ወንጀል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያደርሳል፡፡

### 1.7.3 የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ግዴታቸውን እንዲጥሱ ለመንግስት ባለስልጣን በማማለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት በወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑ አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው፡፡ እነዚህ የመንግስት ባለስልጣንና አላግባብ በዝርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ ለማድረግ አቅም የሚሰጣቸው ነው፡፡ ወንጀሉን ለማጋለጥ የሚፈልጉትን በማባበል እንቢ ካሉም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩ እንዳይጋለጥ ለማድረግና ተድበስብሶ እንዲቀር ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ፣ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት ከባድ ነው፡፡

### 1.7.4 በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ይኖራል፡፡ ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ የደረሰበትን በደል ለመካስ ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል፡፡ በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በወንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ፡፡ በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጂ ሊያጋልጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክኒያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

“የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም” የሚል አባባል አለ፡፡ የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል፡፡ በአንጻሩ በአገርና በዝዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ

የሚያደርግ ሰዉ ላይገኝ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅጉ ብዙ ነዉ፡፡

### 1.7.5 ድንበር ተሻጋሪነቱ

ሰዎች የሙስና ወንጀል የሚፈጽሙበት ዋነኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ፡፡ በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመጓዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብርተኝነት ለመሳሰሉ ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ትስስር በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል፡፡

## 1.8 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

### 1.8.1 በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር (በማድረግ) ወይም በግድፈት (ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.2 ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ ፣የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

በንግድ ዘርፍ ውስጥ የሚከሰት ጉቦ በተለያየ አይነት እንደሚከሰት ጥናቶች ያሳያሉ። ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል።

- **ክፍያዎችን ማመቻቸት** (Facilitating Payments)፡- ይህ የጉቦ አይነት ባለሥልጣናት መደበኛ ተግባራቸውን በፍጥነት ወይም በብቃት እንዲያከናውኑ በሚል የሚከፈሉ ክፍያዎች ናቸው። ክፍያዎችን ማመቻቸት ምንም ጉዳት የሌለው ቢመስልም፣ በህጋዊ እና ህጋዊ ባልሆኑ ክፍያዎች መካከል ያለውን መስመር ሊያደበዝዝ እና ይበልጥ አሳሳቢ ወደሆነ የጉቦ ስልቶች የሚያሳልጥ መንገድ ሊፈጥር ይችላል።
- **ምዝበራ** (Extortion)፡- ይህ የጉቦ አይነት በዛቻ ወይም በማስገደድ ከንግድ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ገንዘብ ወይም ንብረት መውሰድና መጠቀምን ያካትታል። ይህ ወንጀል በመንግስት ባለስልጣናት፣ በተደራጁ የወንጀል ቡድኖች ወይም በሌሎች ተዋናዮች ሊፈጸም ይችላል። ይህም ፍርሃት እና የማስፈራራት ሁኔታን በመፍጠር፤ ህጋዊ የንግድ እንቅስቃሴን ያዳክማል። :
- **የንግድ ልውውጥ ጉቦ** (Commercial Bribery)፡- ይህ በንግድ ልውውጦች ላይ ፍትሃዊ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በንግድ ድርጅቶች መካከል ጉቦ መለዋወጥን ያካትታል። ለምሳሌ የተፎካካሪን ድርጅት ሚስጥራዊ መረጃ ለማግኘት ጉቦ መስጠት፣ አቅራቢው ዝቅተኛ ዋጋ እንዲያስገኝ ጉቦ መስጠት፣ ወይም ደንበኞች የአንድን ድርጅት ምርት እና/ወይም አገልግሎት ያለአግባብ እንዲመርጡ እና እንዲገዙ ጉቦ መስጠትን ያካትታል።

### 1.8.3 የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.8.4 አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)

ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ ፣የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ ፣ ንብረት ጠባቂ ፣ወይም አጣሪ ፣ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን

የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) ፣ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ለማድረግ ጉዳ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም ተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

**1.8.5 የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)**

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ፦

በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤

በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡
፡

**1.8.6 አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)**

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፦

የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 1.8.7 በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም፦

የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም

የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.8.8 በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፦

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤

በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣የንግድ ስምምነት፣የስራ ጨረታ፣የዕቃ ማቅረብ ዉል ፣ወይም ሌላ ጥቅም ወይም

በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን ፣ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.8.9 በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፡-

ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤ ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረከብበት ወይም

በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.10 ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ፣በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ፣ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.11 ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (አንቀፅ 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡

### 1.8.12 ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ ወይም እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.13 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤ ያለዉ ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል።

### 1.8.14 የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)

አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ፣ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ ፣ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.8.15 መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)

ማንኛዉም ሰው  የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፤

አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤

በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ ፣ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.8.16 መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24)

ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ ፣የቀደደ፣ ያጠፋ ፣ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.17 ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (አንቀፅ 26)

ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ ፣የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠቅም፡፡

### 1.8.18 ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25)

ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዉ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.19 ማቀባበል (አንቀፅ 27)

ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ ፣ዋጋ ያለዉ ነገር ፣አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይመ ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ፣ያገናኘ ፣ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.8.20 በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤ ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፣

### 1.8.21 በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣  ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል፡፡ ሰጭዉም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ  ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል፣

### 1.8.22 በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)

ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እነዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.8.23 ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ፤መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም፡፡

### 1.8.24 ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ፡፡

### 1.8.25 በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

ከተጠቀሱት 25 የሙስና ወንጀሎች በተያየዘ በንግዱ ዘርፍ አሰራር ውስጥ የሚከሰቱ የሙስና ዓይነቶች የተለየ መልክ ሊኖረው ይችላል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

➢ **ማጭበርበር** (Fraud)

የተንሰራፋ እና ጎጂ የሙስና አይነት የሆነው ማጭበርበር በኢትዮጵያ የንግድ ዘርፍ ላይ ጥላ ሲያጠላ ቆይቷል፡፡ ይህ ድርጊት የኢኮኖሚ እድገትን ያሳጣል፣ እምነትን የሚሸረሽር እና ዘላቂ ልማትን የሚያደናቅፍ ነው፡፡ ማጨበርበር በንግድ ዘርፍ ውስጥ በሚከተሉት አይነት ሊከሰት ይችላል፤ ሲከሰትም ቆይቷል፡፡

- **የተጭበረበረ ሰነድ፡-** ይህ ድርጊት ከጉምሩክ ቀረጥ ለመሸሽ፣ ተመራጭ የንግድ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ወይም ሕገወጥ ድርጊቶችን ለመደበቅ የተጭበረበሩ ሰነዶችን መጠቀምን ያካትታል፡፡ ለምሳሌ፡- ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎችን ዋጋ አሳንሶ የውሸት ደረሰኞችን ማስገባት፣ ለቅድመ አያያዝ ለመጠየቅ የተጭበረበሩ የትውልድ ሰርተፍኬቶችን መጠቀም ወይም ሐሰተኛ ኩባንያዎችን በህገወጥ ንግድ እንዲሰማሩ መፍጠርን ያካትታሉ፡፡
- **የንግድ እቃዎች የተሳሳተ መግለጫ፡-** ይህ ከፍ ያለ ታሪፍ፣ ኮታ ወይም ሌሎች የንግድ ገደቦችን ለማስቀረት ሆን ተብሎ ሸቀጦችን በተሳሳተ መንገድ መከፋፈል ወይም ማዛባትን ያካትታል፡፡ ለምሳሌ፡- ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸውን ከውጪ የሚገቡ እቃዎች ላይ ቀረጥ ለማስቀረት

ከፍተኛ ዋጋ ማወጅ፣ አደገኛ ቁሳቁሶችን ከደህንነት ደንቦች ለማምለጥ ወይም የተከለከሉ ዕቃዎችን በህጋዊ ጭነት ውስጥ መደበቅን ያካትታሉ።

- **ኮንትሮባንድ፡-** ይህ ድርጊት የሚፈለገውን ቀረጥ ወይም ታክስ ሳይከፍል በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ወደ ውጭ መላክን ያካትታል። ኮንትሮባንድ ብዙውን ጊዜ የተደራጁ የወንጀል መረቦችን ያካትታል እና ለሕጋዊ የንግድ ድርጅቶች ፍትሃዊ ያልሆነ ውድድርን ጨምሮ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ መዘዞችን ያስከትላል።
- **በንግድ ላይ የተመሰረተ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር፡-** ይህ ህገወጥ የገንዘብ እንቅስቃሴ ህጋዊ ለማስመሰል የንግድ ግብይቶችን መጠቀምን ያካትታል። ለምሳሌ፡- ህገወጥ ገንዘቦችን በድንበር ለማዘዋወር፣ የሸቀጦችን እውነተኛ ባለቤትነት ለመደበቅ የውጭ ኩባንያዎችን መጠቀም፣ ወይም በህገወጥ የገንዘብ ማዘዋወሪያ መሳሪያዎች (እንደ ክሬዲት ደብዳቤ) በመጠቀም ለሸቀጦች ከመጠን በላይ ወይም በታች መጠየቂያ መላክን ያካትታሉ።
- **የሳይበር ወንጀል ንግድ፡-** ይህ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ በንግድ ዘርፍ ማጭበርበርን ያካትታል። ለምሳሌ፡- የንግድ መረጃዎችን ለመቀየር የጉምሩክ ስርአቶችን ሰብሮ መግባት፣ የኦንላይን ገበያ በመጠቀም ሸማቾችን ማጭበርበር ወይም አስቸሪ ኢሜይሎችን በመጠቀም ሚስጥራዊነት ያለው የንግድ መረጃን መጠቀም ያካትታ።

➢ **በሰዎች/በተቋማት መካከል የሚደረጉ ህገወጥ የገበያ ስምምነት** (Collusion)

በነጋዴዎች፣ በባለሥልጣናት እና በሌሎች ተዋናዮች መካከል የሚስጥር ስምምነቶችን ወይም ሴራዎችን የሚያካትት የሙስና ዓይነት ሲሆን ገበያን በማዛባት ንግድን ለግል ጥቅማቸው ለማዋል፣ ሸማቾችን መጉዳት፣ ፉክክርን ማፈን እና የኢኮኖሚ ልማትን ማዳከምን ያካትታል። ይህ አይነት ወንጀል በሚከተሉት መልክ ሊከሰት ይችላል።

- **ዋጋ ያለአግባብ መወሰን** (Price fixing)፡ ተፎካካሪዎች ሰው ሰራሽ በሆነ መንገድ ለሸቀጦች ወይም አገልግሎቶች ዋጋ ለማዘጋጀት እንዲሁም ሸቀጦችን ወይም አገልግሎቶችን በመያዝ/በማቆየት ላለመሸጥ መተባበርን የሚያካትት ሲሆን ይህም ድርጊት በተጠቃሚዎች ላይ መጉላላት እና ከፍተኛ ወጪን የሚያስከትል፤ ፈጠራንም ይቀንሳል።
- **የጨረታ ማጭበርበር** (Bid Rigging)፡ ኩባንያዎች በመንግስት ግዥ ሂደቶች ላይ ጨረታን ለማጨበርበር ይተባበራሉ፣ ይህም አስቀድሞ የተወሰነ ኩባንያ የጨረታው ጥራት እና ዋጋ ምንም ይሁን ምን አሸናፊ መሆኑን በማረጋገጥ ለመንግስት ፕሮጀክቶች የዋጋ ንረት እና የውጤታማነት መቀነስ ያስከትላል።

- **የገበያ ድልድል** (Market Allocation)፡ ተፎካካሪዎች ገበያን በመካከላቸው ይከፋፈላሉ፣ ደንበኞችን ወይም የገቢያ ክልሎችን እርስ በእር በስምምነት በመመደብ ትክክለኛና ቀጥታኛ ውድድርን ለማስቀረት የሚደረግ ተግባር ነው፡፡ ይህም ድርጊት የሸቀጦችና አገልግሎቶች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር ያደርጋል፣ የፈጠራ ውስንነት ያስከትላል፡፡
- **አቅራቦት/አገልግሎት መገደብ** (Supply/service Ristrictions)፡ ኩባንያዎች የምርት ወይም የአገልግሎት አቅርቦትን ለመገደብ ይተባበራሉ፣ ይህም ዋጋ ለመጨመር ሰው ሰራሽ እጥረት በመፍጠር ለተጠቃሚዎች ከፍተኛ ዋጋ እና የአቅርቦት መቀነስ ያስከትላል፡፡

➢ **ምዝበራ** (Embezzlement)

ምዝበራ የንግዱን ዘርፍ በመሚመሩ ባለሥልጣናት፣ ሠራተኞች ወይም በንግድ ሥራ አስፈፃሚዎች የሚፈፀም የሙስና ዓይነት ሲሆን ለንግድ ነክ ተግባራት የታቀዱ ገንዘብን፣ ዕቃዎችን ወይም ሀብቶችን ያለአግባብ መበዝበዝ ወይም መስረቅን ያካትታል፡፡ ይህ በአብዛኛው የሚከሰተው በእምነት ቦታ ላይ ያሉ ግለሰቦች ንብረቶችን ለግል ጥቅም ወይም ለገንዘብ ጥቅም ሲቀይሩ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የንግድ ዘርፍ አሰራር ውስጥ ምዝበራ በተለያዩ መንገዶች ሊከሰት ይችላል፡፡

- **የመንግስት ገንዘብ መሰወር፡-** ባለስልጣናት ለንግድ ልማት የተመደበውን እንደ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች፣ የአቅም ግንባታ ወይም ለአነስተኛ ንግዶች ድጎማ ተብለው የሚመደቡ ገንዘቦችን ሊሰውሩ ይችላሉ፡፡
- **ዕቃዎችን አላግባብ መሰወር፡** ነጋዴዎች ወይም የጉምሩክ ባለሥልጣኖች ዕቃዎችን በማከማቻ፣ በማጓጓዝ ወይም በምርመራ ወቅት ለግል ጥቅም ሊሸጡ ይችላሉ፡፡
- **ዋጋ ግሸበት እንዲኖር ማድረግ፡-** ነጋዴዎች እና የመንግስት ባለስልጣናት በግዥ ውል ውስጥ የሸቀጦችን ወይም አገልግሎቶችን ዋጋ በመጨመር ትርፍ ገንዘብ ሊወስዱ ይችላሉ፡፡

➢ **ኔፖቲዝም** (Nepotism)

የኔፖቲዝም ሙስና የሚከሰተው በስልጣን ላይ ያሉ ግለሰቦች ለቤተሰብ አባላት ወይም ለቅርብ ጓደኞቻቸው ቅድሚያ ሲሰጡ ነው፡፡. ይህ ዓይነቱ አድሎአዊነት ፍትሃዊነትን፣ ፉክክርን እና ቅልጥፍናን በማሳጣት ብቁ ያልሆኑ ወይም ብቃት የሌላቸውን ግለሰቦች ቁልፍ በሆኑ የስራ

መደቦች በቅጥር ወይም በሹመት መቅጠርን ወይም መመደብን ያካትታል፡፡ በኢትዮጵያ ንግድ ዘርፍ የዘመድ አዝማድ ሙስና በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል፡፡

- **የውግንና ቅጥር፡** በንግድ ተቆጣጣሪ አካል ውስጥ ያለ ከፍተኛ ባለስልጣን ምንም እንኳን ብቃት ባይኖራቸውም የቤተሰብ አባልን ወይም ጓደኛን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ሊሾም ይችላል፡፡ ይህ የንግድ አስተዳደርን ውጤታማነት ሊያደናቅፍ ይችላል፣ ምክንያቱም ውሳኔዎች ከዕውቀት ይልቅ በግል ታማኝነት ላይ የተመሰረቱ ሊሆኑ ይችላሉና፡፡
- **የውግንና ኮንትራት መስጠት፡** ለህዝብ ግዥ ኃላፊነት የሚወስዱ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በዘመዶቻቸው ወይም በቅርብ አጋሮቻቸው ባለቤትነት ለተያዙ የንግድ ሥራዎች ትርፋማ ውሎችን ሊሰጡ ይችላሉ፣ ምንም እንኳን እነዚህ የንግድ ሥራዎች ምርጥ እጩ ባይሆኑም፡፡ ይህ ድርጊት ወደ የተጋነነ ወጪ፣ ደረጃውን ያልጠበቀ አገልግሎት/ምርት አቅርቦት ወይም ኢ-ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- **ጉሙሩክ እና ፍቃድ፡-** በኢትዮጵያ የንግድ ፍቃድ ወይም የጉምሩክ ባለስልጣን ውስጥ ያለ አንድ ባለስልጣን ልዩ የንግድ ፍቃድ፣ ወይም ምቹ የጉምሩክ ሂደት ለቤተሰብ አባላት፤ ለጓደኞቻቸው ወይም ለጥቅም አጋራቸው ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህም መደበኛ አሰራርን እና ደንቦችን እንዲተላለፉ ያስችላቸዋል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አመቻቹ በሚያደራጁት ቡድን መሰረት ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. “ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት” በዘርፋችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉ፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤
2. በዘርፉ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. “ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀል” ን ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ፡፡

***ከዚህ በታች የቀረቡትን ሁለት ኬዞች በማንበብ እና ከቡድን አባላት ጋር በመወያየት ለጥያቄዎቹ ምላሽ ስጡ፡፡***

***ኬዝ አንድ፥***

*በኢትዮጵያ የንግድና ቀጠናዊ ትብብር ሚኒስቴር የወጪና ገቢ ዕቃዎችን እንዲሁም በአገር ውስጥ የሚመረተውን የፋብሪካ ምርቶችን የጥራት ቁጥጥር የመቆጣጠር ኃላፊነት የስራ እንቅስቃሴ ውስጥ ሥነ ምግባር የጎደለው አገልግሎት የመነጨ ተደጋጋሚ የሥራ መቆራረጥ እና የደንበኞች ቅሬታዎች ተስተውለዋል፡፡ በወጪና ገቢ ንግድ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች እንዲሁም የሀገር ውስጥ አምራቾች የአገልግሎት መዘግየት እና የጉቦ ክፍያ ስጋት በተደጋጋሚ ገጥሟቸዋል፡፡ አንዳንድ ኩባንያዎች የጥራት ቁጥጥር ሂደቱን ለማፋጠን ባለስልጣኖች ክፍያዎችን እንደሚጠይቁ ይናገራሉ፡፡ እነዚህ ከሥነ ምግባር ውጪ የሆኑ ድርጊቶች በንግድ ድርጅቶች ላይ ከፍተኛ ኪሳራ አስከትለዋል እና በሚኒስቴሩ አገልግሎት ታማኝነት ላይ ሰፊ ስጋት ፈጥረዋል፡፡ (ምንጭ፡ Dawit Mesfin, [8/23/2024 4:43 AM]).*

***ጥያቄ፡***

- ***ከላይ በኬዙ በተጠቀሰው መስራት የተከሰተውን የሙስና ዓይነት እና እንዴት ሊከሰት እንደቻለ ግልጹ፡፡***

***ኬዝ ሁለት፡***

*በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ የእርሻ ምርቶች የወጪ ንግድ ግብይት ኃላፊና ሌሎች የላይሰንሲንግና ሬጉላቶሪ መሪ ሥራ አስፈጻሚ የሥራ ሂደት ውስጥ ተመድበው ሲሠሩ የነበሩ ሰራተኞች ያልተገባ ጥቅም ለራሳቸው ለማግኘት በማሰብ በ2016 ዓም በስራ ኃላፊነታቸው ምክንያት የብቃትና የማቅረብ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ የሚጠየቅበትን የጫት ላኪነት የምስክር ወረቀት የማጽደቅና የመጫን ተግባር እንዲያካሂዱበት በአደራ በተሰጣቸዉ የኦንላየን አገልግሎት የመረጃ መረብ ላይ በተለያዩ ቀናት ለተለያዩ ድርጅቶች ከንግድና ትስስር ዘርፍ የጫት ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይሰጣቸዉ እንደተሰጣቸዉ በማስመሰል ሀሰተኛ የጫት ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስከር ወረቀት በማጽደቅ አና ኦንላየን በመጫን ብቃት ለሌላቸዉ ነጋዴዎች ህገ-ወጥ የጫት ላኪነት ንግድ ፍቃድ እንዲያገኙ በማድረግ የአሠራር ሥርዓትን በመጣስ በመንግሥት ሥራ ላይ በደል በማድረስ እና ሀሰተኛ ፈቃድ በመስጠት የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 70 (1) እና (14) ድንጋጌዎችን ተላልፈው እንደተገኙ ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡*

***ጥያቄ፡ ኬዙን በመረዳት የተከሰቱ የሙስና አይንቶችን ለዩ፡፡ የተከሰተው ሙስና በምን ሁኔታ እንደተከሰተ አብራሩ፡፡***

# ምዕራፍ ሁለት

# የንግድ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት

## 2.1 መግቢያ፣

በአጠቃላይ ማንኛውም ተቋም ወይም ዘርፍ ለሙስና ተጋላጭ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የተቋማት የተጋላጭነት ደረጃ እና ሁኔታ ሊለያይ እንደሚችል ይታመናል። በዚሁ መሰረት የንግዱ ዘርፍም ለሙስና በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ ናቸው ከሚባሉት ተቋማት አንዱ ነው። ዘርፉ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት በተመለከተ እና የሚያስከትለው ጉዳት በዚህ ምዕራፍ በዝርዝር ቀርቧል።

## 2.2 የምዕራፉ ዓላማ፤

ሰልጣኞች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኃላ፤

- ሙስና በሁሉም ሀገራት እና ተቋማት ሊከሰት እንደሚችል ይገነዘባሉ፤
- የንግድ ዘርፍ ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት በመረዳት በትክክል ያብራራሉ፤

## 2.3 የተፈቀደው ጊዜ፤

ይህን ምዕራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 4:00 ሰዓት ነው።

## 2.4 ስለ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አጭር ማብራሪያ

ለአንድ ሀገር እድገት አስተዋፅዎ ከሚያደርጉ ዘርፎች መካከል አንዱ የንግድና ቀጠናዊ ትስስ ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚንስቴርን ጨምሮ ሰባት ተቋማትን በማቀናጀት ሀላፊንቱን እንዲውጣ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263 /2014 የተቋቋመ ሲሆን በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን በማመንጨት ተግባራዊ ያደርጋል። ንግድ በህጋዊ መሰረት እንዲስፋፋና እንዲዘምን ይሰራል፤ በክልሎች መካከል የሚደረግን የንግድ ግንኙነት ይመራል፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጥበትን ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤ የወጪና ገቢ ንግድ

ዕቃዎችን ጥራት ይቆጣጠራል፤ የወጪና ገቢ ዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመገዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት ይዘረጋል፤ የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ በማውጣትና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ ሲፈቀድ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤ የንግድና የዘርፍ ማህበራት እና የሸማቾች ማህበራት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩም ያደርጋል፤የሀገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓት ለመተግበር እንዲቻል አስፈጻሚ አካላትን በማስተባበር የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፤ የታቀደውን እድገት ለማምጣት የሚያስፈልጉ ጥናትና ምርምሮች ይተገብራል፤ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን በመስጠት ለተሰጠባቸው ዓላማ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤ የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ሥራን ይሠራል፤ በአዋጅ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን የተሰጡ ከዳኝነት ችሎት ሥራ ውጪ ያሉ ተግባርና ኃላፊነቶችን በሥራ ላይ ያውላል፡፡ እንዲሁም በንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ለንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ተሰጥተው የነበሩ ከዳኝነት ችሎት ሥራ ውጪ ያሉ ተግባርና ኃላፊነቶችን በሥራ ላይ ያውላል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን ስልጣንና ተግብራት ለማከናወን በአዋጁ የተጠቀሱት ሰባቱ ተቋማት የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚንስቴር፣ የኢትዩጵያ ምርት ገበያ፣ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስትቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ተስማምነት ምዘና ኢንስትዩት፣ የኢትዮጵያ አክረዲቴሽን ድርጅት፣ የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ስነ ልክ ኢንስትዩት ናቸው፡፡

የዘርፉን ስልጣንና ተግባራት በማከናወን ሂድት ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የውጤታማንት ጋሬጣ መሆናቸውን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በንግዱ ዘርፍ የሚከሰቱ የሙስና አይንቶች እና የተጋላጭነት ሁኖታና መጠን መሚቀጥለው ተዳሰዋል፡፡

## 2.5 የማነቃቂያ ጥያቄ

*ውድ ሰልጣኞች፡-*

- *የንግድ ዘርፍ ለሙስና ያለውን ተጋላጭነትን ምን ያህል ያውቃሉ?*

### 2.6 የንግዱ ዘርፉ የሙስና ተጋላጭነት

የኢትዮጵያ የንግድ ዘርፍ ከፍተኛ ችግር ያለበት ዘርፍ መሆኑን ብዙ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ዘርፉ በርካታ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፉ እና በሌሎችም ምክኒያቶች ውስብስብ ከመሆኑ ባሻገር ለተለያዩ ሙስና ዓይነቶች የመጋለጥ ዕድሉ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ንግድ ዘርፍ ውስጥ የሚስተዋሉ ዋና ዋና የሙስና ተጋላጭነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

#### 2.6.1 ለንግድ ነክ መሠረተ ልማት የመንግስት ግዥ ሂደቶች

በተለይ ከንግድ ጋር የተያያዙ መሠረተ ልማቶች እንደ ወደቦች፣ መንገዶች፣ የባቡር መስመሮች እና የሎጂስቲክስ ተቋማት ያሉ ውሎች ለሙስና ተጋላጭ ናቸው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ፣ የእነዚህ ፕሮጀክቶች ውስብስብነት እና ለተሳተፉት ከፍተኛ ጥቅም ሊኖር ስለሚችል ነው፡፡ ከንግድ ነክ መሠረተ ልማት ውል ውስጥ የተለመዱ የሙስና ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- ***የጨረታ ማጭበርበር፡-*** በተጫራቾች መካከል የሚደረግ ስምምነት አንዱ በተጋነነ ዋጋ ውል እንዲያገኝ ማድረግ፡፡
- ***አድልዎ-*** ብቃታቸው ወይም ዋጋቸው ምንም ይሁን ምን ለንግድ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ግላዊ ግንኙነት ላላቸው ኮንትራቶችን መስጠት፡፡
- ***ምዝበራ፡*** ለመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የተመደበውን ገንዘብ አላግባብ መበዝበዝ፡፡
- ***ጉቦ፡-*** በውል አሰጣጥ ላይ ተጽእኖ ለማድረግ ክፍያዎችን መስጠት ወይም መቀበል፡፡

#### 2.6.2 የንግድ ፈቃድ መስጠት እና የፈቃድ መስጠት ሂደት

የንግድ ሥራ ፈቃድ ግለሰቦች እና ድርጅቶች በንግዱ ዘርፍ እንዲሰማሩ አስፈላጊ ነው፡፡ የንግድ ፈቃድ እና ፈቃድ መስጠት የንግድ ደንቡ ወሳኝ ገጽታ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሂደት ለሙስና የተጋለጠ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ባለሥልጣኖች ጉቦ ሊጠይቁ ወይም ለተወሰኑ ግለሰቦች ወይም የንግድ ድርጅቶች ሊያደሉ ይችላሉ፡፡ በንግድ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ለሙስና አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ምክንያቶች፡-

- **ልዩ ሥልጣን**፡- ፈቃድ የሚሰጡ ባለሥልጣኖች ብዙውን ጊዜ ሰፊ ልዩ ሥልጣን አላቸው፣ ይህም ለግል ጥቅም አላግባብ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡
- **ግልጽነት የጎደለው አሰራር፡-** ፍቃድ የማግኘት ሂደት ግልጽነት የጎደለው ሊሆን ስለሚችል ሙስናን ለመከታተልና ለመለየት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

- **ውስብስብ አካሄዶች፡-** የፈቃድ ማመልከቻ ሂደት ውስብስብ እና ጊዜ የሚወስድ ሊሆን ይችላል፣ ይህም ጉቦ የመሰብሰብ እና የመበዝበዝ እድሎችን ይጨምራል።
- **የኢኮኖሚ ምክያቶች፡-** የንግድ ድርጅቶች ለትርፍ ሲሉ ፈቃድ ለማግኘት ብልሹ አሰራር ውስጥ ይገባሉ።
- **የቁጥጥር ድክመቶች፡-** የንግድ ደንቦችና ፖሊሲዎች ደካማ አፈጻጸም ለሙስና ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።
- **የንግድ ድንበር ተሻጋሪነት፡-** የንግድ ወሰን ተሻጋሪ ባህሪ ከፈቃድ አሰጣጥ ጋር የተያያዙ የሙስና ጉዳዮችን ለመመርመር እና ለህግ ለማቅረብ አስቸጋሪ ያደርገዋል።

### 2.6.3 የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት (FDI) ሂደቶች

የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ጉልህ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ምንጭ ሊሆን ይችላል። ሆኖም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ስምምነቶችን የመደራደር እና የመተግበር ሂደት ለሙስና የተጋለጠ ነው። የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ሂደቶች ለሙስና በር የሚከፍቱባቸው መንገዶች፡-

- **ልዩ/ያልተገደበ ሥልጣን፡-** የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ድርድሮች ላይ የሚሳተፉ የመንግስት ባለስልጣናት ብዙ ጊዜ ሰፊ ልዩ/ያልተገደበ ስልጣን አላቸው ይህም ለግል ጥቅም አላግባብ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።
- **ግልጽነት ማነስ፡-** የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ስምምነቶችን በተመለከተ የሚደረጉ ድርድሮች ግልጽነት የጎደላቸው ሊሆኑ ስለሚችሉ ሙስናን ለመቆጣጠር እና ለመለየት አስቸጋሪ ያደርገዋል።
- **ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች፡-** የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማትን መሻት መንግስታት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን እንዳይሳተፉ ያደርጋቸዋል፣ ምንም እንኳን ውሎችን ለማስማማት ብልሹ አሰራር ውስጥ የሚገቡ ቢሆኑም።
- **የቁጥጥር ድክመቶች፡-** ደካማ የቁጥጥር ማዕቀፎች እና የማስፈጸሚያ ዘዴዎች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ሂደቶችን የሙስና አደጋን ይጨምራሉ።
- **ባህላዊ ሁኔታዎች፡-** እንደ ሙስና ወይም ወገንተኝነት ያሉ ሁኔታዎችን በቸልተኝነት ማለፍ የመሳሰሉ ባህላዊ ሁኔታዎች የሙስና ስርጭትን በቀጥታ ኢንቨስትመንት ድርድር ላይ እንዲስፋፊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።

### 2.6.4 ያልተሟላ ተቋማዊ አደረጃጀት

ተቋማት ለሙስናንና ብልሹ አሰራር የተጋላጭንት ሁኔታ ሙሉ ተቋማዊ አደረጃጀት አለመኖር ወይም በቂ ካለመሆን ጋር ጥብቅ ግንኙነት እንዳለው ጥናቶች ያሳያሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ የፌደራል የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2015 ያጠናው ጥናት እንደሚያሳየው በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ የስነ-ምግባር መከታተያ አደረጃጀት በአመዛኙ በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት የተሟላ ቢሆንም በዘርፉ ስር የተደራጁት መከታተያ ክፍሎች የሙስና እና ብልሹ አሰራርን የሚተገብሩት በጊዚያዊነት በውክልና መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የስራ ክፍሉ ቢኖርም በተወሰኑት ላይ የተሟላ የሰው ኃይል እጥረት መኖሩ፣ ለማሳያ ያህል በነዳጅና ኢነርጅ ባለስልጣን እና በተስማሚነትና ምዘና ደርጅት ለጥቆማ አመቺ የሆነ ቢሮ ባለመኖሩና የስራ ቁሳቁስ በማሟላት በኩልም ውስንነት ያለው መሆኑን በምልከታ ታይቷል፡፡ በዘርፉ ውስጥ የኢትዮጵያ አክሪዴሽን አገለግሎት ለክፍሉ የተሰጠ ቢሮም ሆነ ቁሳቁስ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህ እና ሌሎች ምክኒያቶች በዘርፉ የሚከሰተውን ሙስና በአጥጋቢ ሁኔታ ለመከላከል አልተቻለም፡፡

### የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ በተጠናቀቀው ምዕራፍ የንግዱ ዘርፍ ለሙስና ያለውን ተጋላጭነትም በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ለዚህም እንደምክኒያት የተጠቀሱት የቁጥጥር ድክመቶች፤ የጉምሩክ እና የድንበር አስተዳደር ሁኔታ፤ ለንግድ ነክ መሠረተ ልማት የመንግስት ግዥ ሂደቶች፤ የንግድ ፈቃድ እና ፍቃድ መስጠት ሂደት፤ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት (FDI) ሂደቶች፤ የፖለቲካ ተጽዕኖ እና ድጋፍ፤ እና የግብር እና የገቢ አሰባሰብ ሂደቶች ናቸው፡፡

### የማጠቃለያ ጥያቄዎች

*ውድ ሰልጣኞች፡-*

- *የንግድ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት እንዴት ለሙስና አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ተወያዩ፡፡*
- *በገፅ 32 የተመላከተውን ኬዝ በማንበብ እና ከቡድን አባላት ጋር በመወያየት ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ስጡ፡፡*

***ኬዝ ሶስት፡***

*አዲስ እስታንዳርድ በጥቅምት 11/2017 ባወጣው እትም የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት አራት ሰራተኞች በጥቅም በመመሳጠር ምንም አይነት የግዢ ፍላጎት ሳይኖር ከሁለት ፋብሪካዎች 29,200 ኩንታል ሲሚንቶ በዝቅተኛ ዋጋ በመግዛትና በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥ ለግል ጥቅም ማዋል ሙስና ተጠርጥረው ክስ እንደተመሰረተባቸው ያትታል። ሰራተኞቹ ሲሚንቶውን በብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ስም የገዙ ሲሆን በ2013 እ/ኢ/አ በህገ ወጥ መንገድ ከ30 ሚሊየን ብር በላይ ለግል ጥቅማቸው ገቢ ማድረጋቸውን አዲስ እስታንዳርድ አትቷል። ተከሳሾቹ የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት የኮንስትራክሽንና ሎጂስቲክስ ምክትል ዳይሬክተር፣ የኮንስትራክሽንና ሎጂስቲክስ ግዥ መምሪያ ኃላፊ እና ሁለት የግዥ ስፔሻሊስቶች መሆናቸውን የፍትህ ሚኒስቴር መግለጫ አመልክቷል። በ3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ስም ደብዳቤ ተጽፎ በግል ሒሳባቸው እየከፈሉ ነገር ግን በመሥሪያ ቤቱ ስም ግዢ ተፈጽሞ ሲሚንቶው ለግል ፍጆታ በጥቁር ገበያ ተሸጧል። 2ኛ ተከሳሽም 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች 1ኛ ተከሳሽ የፃፉትን ደብዳቤ ለደርባ እና ዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች እንዲያደርሱ እና በተቋሙ ስም የተገዛውን 29,200 ኩንታል ሲሚንቶ እንዲሸጡ አዟል። በመግለጫው መሰረት ተከሳሾቹ በዳኛ ፊት ቀርበው ክሱ እንደተነበበላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሾች ለታህሳስ 07 ቀን 2015 እ/ኢ/አ መቃወሚያቸውን እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል።. ከቆይታ ብኋላ ፤ እንደ ኤፍ ቢ ሲ (ጥቅምት 6፣ 2017) ሪፖርት መሰረት፤ ተከሳሾቹ በተለያዩ ቀናቶች ያቀረቡትን የመከላከያ ማስረጃ የመረመረው ፍርድ ቤቱ 1ኛ ተከሳሽን የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ተቋም የኮንስትራክሽን እና ሎጂስቲክስ ም/ዳይሬክተርና በተቋሙ የግዢ ባለሙያ ናቸው የተባሉ ሁለቱ ተከሳሾች ላይ በተከሰሱበት የሙስና ወንጀል ጥፋተኛ ብሏቸዋል።*

***ጥያቄ፡- የዚህ አይነት ሙስና ተጋላጭነቱን፣ ለሙስና የተጋለጡበትን ሁኔታ፤ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ እና የንግድና ቀጠናዊ ትትስስር ሀላፊንት ላይ ተወያዩ።***

# ምዕራፍ ሶስት

## ሙስና በንግድ ዘርፍ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት እና የመከላከያ ስልቶች

### 3.1 መግቢያ፣

በዚህ ምዕራፍ ሁለት ንዕስ ርዕሶች ሲኖሩት፤ በመጀመሪያው ንዕስ ርዕስ ሙስና በንግዱ ዘርፍ ሚስከትለው ዘርፈ-ብዙ ተጽዕኖ በዝርዝር ይቀርባል፡፡ ሙስና በሁሉም ሀገራት እና ተቋማት ክፍተኛ ኢኮኖዊያሚ፤ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ጉዳት የሚደርስ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፤ በንግዱ ዘርፍም ሚስከትለው ተጽዕኖ ቀላልል የሚባል አይደለም፡፡ በሁለተኛው ንዕስ ርዕስ ደግሞ ሙስናን ለመከላከል የሚጠቅሙ ስልቶች በስፋት ይብራራሉ፡፡

ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው፡፡ ለመከሰቱ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም እንዲሁ በርካታ ናቸው፡፡ ታዲያ ይህን ተለዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ለመዋጋት ዘርፎች እንደየተቋማቸው ባህርይ በየጊዜው የሚሻሻል፣ መጠነ ሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስና መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሙስናን የመከላከል ተግባር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ያለውን ሃገራዊ ሃብት ለታለመለት ሥራ ለማዋል ያስችላል፡፡

ችግሩ ከተከሰተ በኂላ የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ ወጪ ያስቀራል፤ በመንግስት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ በዘርፉ ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስልቶች ይዳሰሳሉ፡፡

### 3.2 የምዕራፉ ዓላማዎች፤

ከዚህ የስልጠና ምዕራፍ መጠናቀቅ በኃላ፡-

- ሰልጣኞች ሙስና በንግዱ ዘርፍ ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ/ጉዳት በተመለከተ ዕውቀት ይኖራቸዋል፤

- የሙስና መከላከያ ስልቶችን ይተነትናሉ፣
- የሙስና መከላከያ ስልቶችን ያወዳድራሉ፣
- የዘርፋቸውን የሙስና መከላከያ ስልቶች ይገመግማሉ፣
- በዘርፋቸው የመከላከያ ስልቶችን ይተገብራሉ፣

## 3.3 የተፈቀደው ጊዜ፤

ይህን ምዕራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 4:00 ሰዓት ነው፡፡

## 3.4 የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤

*ውድ ሰልጣኞች፡*

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ተሳታፊ ጋር በመሆን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. ሙስና በንግዱ ዘርፍ ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ምን ያህል እንደሆነ ያውቃሉ?
2. የምታውቋቸውን የሙስና እና የብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችና ጥቅማቸውን ዘርዝሩ፡ ፡
3. በዘርፋችሁ ተግባራዊ የሚደረጉ ጠንካራ የሙስና መከላከያ ስልቶች ዘርዝሩ፡፡
4. ሙስና እና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስገኘውን ፋይዳ አብራሩ፡፡

## 3.5 ሙስና በንግዱ ዘርፍ የሚያስክትለው ተፅዕኖ/ጉዳት

### 3.5.1 የሙስና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ/ጉዳት

በኢትዮጵያ ንግድ ዘርፍ የሚፈጸመው ሙስና ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ መዘዞችን የሚያስከትል ሲሆን ከነዚህም መካከል፡-

- **የውጭ ኢንቨስትመንትን ይቀንሳል፡-** የሙስና አመለካከት የውጭ ባለሀብቶችን ሊያደናቅፍ ስለሚችል ዝቅተኛ የካፒታል ፍሰት እንዲኖር እና የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡
- **ከፍተኛ የንግድ ወጭ ያስከትላል፡-** ሙስና በጉቦ፣ በብዝበዛ እና በሌሎች ህገወጥ ተግባራት የንግድ ወጪን ይጨምራል፡፡ ይህም የኢትዮጵያን የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነት በመቀነስ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለተጠቃሚዎች ውድ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

- **በአለም አቀፍ ገበያ ያለው ተወዳዳሪነት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል፡-** ሙስና ፍትሃዊ ያልሆነ የመጫወቻ ሜዳ በመፍጠር አዳዲስ ፈጠራዎችን በማደናቀፍ የኢትዮጵያን የንግድ ድርጅቶች በአለም ገበያ ያላቸውን ተወዳዳሪነት ሊቀንስ ይችላል። ይህም ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች እንዲቀንስ እና የገበያ ድርሻ እንዲጠፋ ሊያደርግ ይችላል።
- **የመሠረተ ልማት ግዥ ሙስና፡-** እንደ መንገድና ወደብ ያሉ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ግዥ ሙስና ከፍተኛ ወጪና መጓተትን ሊያስከትል ስለሚችል የንግድና የኢኮኖሚ ልማትን ያደናቅፋል።
- **የታክስ ስወራ፡** ሙስና የታክስ ስወራን ሊያመቻች ስለሚችል የመንግስት ገቢ እንዲቀንስ እና የህዝብ አገልግሎት እንዲቀንስ ያደርጋል።

### 3.5.2 የሙስና ማህበራዊ ተጽዕኖ/ጉዳት

በኢትዮጵያ ንግድ ዘርፍ የሚፈጸመው ሙስና ከፍተኛ ማህበራዊ መዘዞችን የሚያስከትል ሲሆን ከነዚህም መካከል፡-

- **የህዝብ አመኔታ መሸርሸር፡-** ሙስና ህዝቡ በመንግስት ተቋማት ላይ ያለውን እምነት በመሸርሸር ማህበራዊ አለመረጋጋትን ያስከትላል። በኢትዮጵያ ውስጥ የተንሰራፋው ሙስና ህዝቡ በመንግስት ላይ ያለውን አመኔታ ያሳጣ እና ለማህበራዊ ውጥረት አስተዋጽኦ አድርጓል።
- **ኢ-እኩልነት መጨመር፡** ሙስና ከስልጣን ጋር ግንኙነት ያላቸውን በሰፊው ህዝብ ኪሳራ ተጠቃሚ በማድረግ ኢ-እኩልነትን ሊያባብስ ይችላል። ኢትዮጵያ ውስጥ ሙስና በሀብታምና በድሆች መካከል ያለውን ልዩነት እንዲሰፋ አስተዋጽኦ አድርጓል።
- **ቀጣናዊ ትስስር ጥረቶችን ያስተጓጉለል፡-** ሙስና ለንግድና ኢንቨስትመንት እንቅፋት በመፍጠር ቀጣናዊ ትስስር ጥረቶችን ሊያደናቅፍ ይችላል። ኢትዮጵያ ውስጥ ሙስና አገሪቱ እንደ አፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና (AfCFTA) በመሳሰሉ ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ቡድኖች ውስጥ እንዳትገባ እንቅፋት ሆኗል።
- **የአስፈላጊ አገልግሎቶች ተደራሽነት መቀነስ፡-** ሙስና ሀብቶችን ከአስፈላጊ ከሆኑ አገልግሎቶች ማለትም እንደ ትምህርት እና ጤና አጠባበቅ ውደ ሙስና ውስጥ ለሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት የግል ጥቅማጥቅሞችን ማዞር ይችላል። ይህም ወደ ልዩነት እና ማህበራዊ አለመረጋጋት ሊያመራ ይችላል።

- **የወንጀል መጨመር፡-** ሙስና ለወንጀል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣ ምክንያቱም ሙሰኛ ባለስልጣናት ህግን የማስከበር እድላቸው አነስተኛ ነው።
- **የፖለቲካ አለመረጋጋት ይፈጥራል፡-** ሙስና የህዝብን አመኔታ በመሸርሸር እና ማህበራዊ ቅሬታን በማባባስ የፖለቲካ መረጋጋትን ሊያዳክም ይችላል።

### 3.5.3 የሙስና ህጋዊ እና ተቋማዊ ተፅዕኖ/ጉዳት

ሙስና በሕግም ሆነ በተቋማት መዋቅር ላይ ትልቅና ጎጂ ውጤት አለው። ተፅዕኖው በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከኢኮኖሚ ልማት እስከ ሰብአዊ መብቶች ድረስ ይሰማል።

#### 3.5.3.1 የሙስና ህጋዊ ተጽዕኖ

- **የህግ የበላይነትን ማናጋት፡-** ሙስና የፍትሃዊነት፣ የእኩልነት እና የተጠያቂነት መርሆዎችን ስለሚሸረሸር የህግ የበላይነትን መሰረት ያናጋል። ሕጎች ሊገዙ ወይም ችላ ሊባሉ በሚችሉበት ጊዜ የሕግ ሥርዓቱ ከፍትህ ጠባቂነት ይልቅ የኃያላን መሣሪያ ይሆናል።
- **የፍትህ ስርዓቱን ማደናቀፍ፡-** በፍትህ አካላት ውስጥ የሚፈጠር ሙስና ወደ ወገንተኝነት ውሳኔ፣ የተሳሳተ ፍርድ እና የፍትህ መዘግየት ያስከትላል። ይህም ህብረተሰቡ በህግ ስርዓቱ ላይ ያለውን አመኔታ ከማሳጣት ባለፈ ፍርድ ቤቶች ህግን በብቃት የማስከበር አቅምን ያደናቅፋል።
- **የተደራጁ ወንጀሎችን ማመቻቸት፡-** በሙስና የተዘፈቁ ባለስልጣናት ህገወጥ ተግባራትን በመጠበቅ ወይም በማመቻቸት ላይ ስለሚሳተፉ ሙስና ለወንጀል ድርጊቶች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ይህ የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውርን፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን እና ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ጨምሮ የወንጀል መጠን መጨመር ሊያስከትል ይችላል
- **የህግ ማስከበር ሂደትን ማዳከም፡-** ህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች በሙስና ሲታከሱ ወንጀሎችን በመመርመር እና በመክሰስ ረገድ ውጤታማነታቸው አናሳ ይሆናል። ይህ ያለመከሰስ ስሜት ሊፈጥር እና ወንጀለኞችን ሊያበረታታ ይችላል።

#### 3.5.3.2 የሙስና ተቋማዊ ተጽዕኖ

- **በተቋማት ላይ ያለው እምነት መሸርሸር፡-** ሙስና ባለስልጣናት የህዝብን ጥቅም አስጠብቀው የሚሰሩ ናቸው የሚለውን እምነት የሚሸረሽር በመሆኑ ህዝቡ በመንግስት

ተቋማት ላይ ያለውን እምነት ያሳጣል። ይህ ወደ ማህበራዊ አለመረጋጋት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት እና የዜጎች ተሳትፎ መቀነስ ያስከትላል።

- **ብቃት የጎደለው አስተዳደር፡-** ሙስና የመንግስት ተቋማትን ቅልጥፍና እና ውጤታማነት ሊያደናቅፍ ይችላል፣ምክንያቱም ለግል ጥቅማጥቅም ሲባል ሃብቶች በአግባቡ ሊያዙ ወይም ሊዘዋወሩ ይችላሉ። ይህ ደግሞ የአገልግሎት አሰጣጡን መጓተት፣የህዝብ አገልግሎት ጥራት ማነስ እና የኢኮኖሚ ልማት ማሽቆልቆልን ያስከትላል።
- **በተጋላጭ ቡድኖች ላይ ያለው ያልተመጣጠነ ተፅዕኖ፡** ሙስና ተመጣጣኝ ባልሆነ ሁኔታ ተጋላጭ ቡድኖችን ማለትም ድሆችን፣ የተገለሉ ማህበረሰቦችን እና አናሳዎችን ሊጎዳ ይችላል። እነዚህ ቡድኖች የፍትህ እና የህዝብ አገልግሎቶች ተደራሽነት ውስን በመሆኑ ለብዝበዛ ተጋላጭ ያደርጋቸዋል።

በአጠቃላይ የሙስና ህጋዊ እና ተቋማዊ ተፅዕኖ ሰፊ ነው። የሕግ የበላይነትን ያዳክማል፣ በተቋማት ላይ ያለውን እምነት ይሸረሽራል፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ያደናቅፋል፣ በተጋላጭ ወገኖች ላይ ያልተመጣጠነ ተፅዕኖ ይፈጥራል።

## 3.6 የሙስና መከላከያ ዘዴዎች፡

በንግዱ ዘርፍ የሚስተዋለውን ሙስና ለመከላከል የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም አስፈላጊ ነው፡ ፡

### 1. የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የዘርፉን የሰው ሃይል በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው። ሰራተኞች የተቋማቸውን ራዕይና ተልእኮ እንዲሁም እሴት ጠንቅቀው ሊያውቁ ይገባል። ተቋማቸው የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል። በተለይ ሰራተኞች ስራቸውን ስነ-ምግባርን የተላበሰ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በሥነ-ምግባራር ጉዳይ ላይ አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው። ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል።

## 2. ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን

ግልፅነት እና ተጠያቂነት የመልካም አስተዳደርን መሰረት ያደረጉ መሰረታዊ መርሆች ናቸው፡፡ ቀልጣፍ እና ውጤታማ ስራን ላማሳካትም ግልፅነት እና ተጠያቂነት ወሳኝነት አላቸው፡፡

### 2.1 ግልጽነት

የግልጽነት ጉዳይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃን ለዜጎች የማድረስ ጉዳይ ነው፡፡ ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻሉ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆኑም፡፡

ዘርፎች በሴክተሩ የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በመንግስት አሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ዜጎች የሚፈልገውን መረጃ በሚፈልገው ወቅትና መጠን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም፡፡

### 2.2 ተጠያቂነት

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት /በቅጣት ወይም ካሳ በመክፈል/ ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራህም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡ ፡ ተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ ባግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል፡፡

### 3. የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውሰጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የተቋሙ ሪሶርስ (ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡

የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡

### 4. የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ

በየዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት ለመለየት ያስችላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል፡፡

### 5. የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ከመንግስት ወይም ከህዝብ ተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ

ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው፡
፡

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል፡፡

ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

## 6. የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ

የፀረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም፡፡ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፓርትና የውጤት ግምገማ አካላቸው ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፡፡ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

## 7. የዘርፉን የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋማቸው ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም ሚና እንዳለቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት መፈፀም ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

- በተቋሙ ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፣

- ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋሙ ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፣
- ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋሙ ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፣
- የጥቅም ግጭትን የመከላከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድ እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፣
- በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፣
- በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት፣

## 8. ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው እንቅስቀሴ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው። ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል። እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል።

## 9. ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው። ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው የመከላከያ ስልት ነው። በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል።

### 9.1 ዲጂታል መንግስታዊ አስተዳደር በዘርፉ ውስጥ መተግበር

- **የኤሌክትሮኒክስ ጉምሩክ መግለጫዎችን መተግበር፡** የኤሌክትሮኒክስ የጉምሩክ መግለጫዎችን መተግበር የሙስና እና የመዘግየት እድልን በእጅጉ ይቀንሳል። ሂደቱን

ዲጂታል በማድረግ ለጉምሩክ ባለሥልጣኖች ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን ለመፈፀም ወይም ሽቀጦችን ለማዘግየት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

- **ሪል-ታይም መከታተል/በጊዜ ግብይት መከታተል**/Real-time Tracking/፦ እንደ ጂፒኤስ እና RFID ያሉ የላቀ የመከታተያ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የጉምሩክ ሂደትን በሚያልፉበት ጊዜ ዕቃዎችን በቅጽበት ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡ ይህም የኮንትሮባንድ ወይም የስርቆት እድሎችን ይቀንሳል፡፡
- **ኦንላይን የክፍያ ሥርዓቶች፦** የኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ሥርዓቶች የጉምሩክ አወጣጥ ሂደቱን በማሳለጥ ከገንዘብ ግብይት ጋር ተያይዞ የሚደርሰውን የሙስና አደጋ ይቀንሳል፡፡

## 9.2. **ለግዥ ዲጂታል መንግስታዊ አስተዳደር መጠቀም** /E-Governance in Procurement

- **የመስመር ላይ የጨረታ መድረኮች**/Online Bidding Platforms/፡ የተማከለ የመስመር ላይ የጨረታ መድረኮች በግዥ ሂደት ውስጥ ግልጽነትን እና ፍትሃዊነትን ሊጨምሩ ይችላሉ፡፡ የጨረታ ሒደቱን ይፋዊና ተደራሽ በማድረግ፣ የመተሳሰብ ወይም የመወዳጀት አቅምን ይቀንሳል፡፡
- **የኤሌክትሮኒክስ ጨረታዎች፡** የኤሌክትሮኒክስ ጨረታዎችን በእውነተኛ ጊዜ ተወዳዳሪ የሆኑ የጨረታ ሂደቶችን ለማካሄድ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፣ ይህም ለገንዘብ የተሻለ ዋጋ መገኘቱን ያረጋግጣል፡፡
- **የአፈጻጸም ክትትል፦** ቴክኖሎጂን በመጠቀም አቅራቢዎችን እና ተቋራጮችን አፈጻጸም በመከታተል የውል ግዴታቸውን እየተወጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

## 9.3. **በቁጥጥር ሂደቶች ውስጥ ዲጂታል መንግስታዊ አስተዳደር መጠቀም**/ E-Governance in Regulatory Processes

- **የመስመር ላይ የፍቃድ ማመልከቻዎች፡** የመስመር ላይ የፍቃድ ማመልከቻዎችን መተግበር የቁጥጥር ሂደቱን ሊያቀላጥፍ እና የሙስና እድልን ይቀንሳል፡፡ የአካላዊ የወረቀት ስራዎችን እና በአካል ተገናኝቶ መስተጋብርን በማስወገድ ለጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ተጽእኖ እድሎችን ይቀንሳል፡፡
- **ደንቦችን ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ፡** መመሪያዎችን በኦንላይን ፖርታል በኩል ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን ይጨምራል፡፡ ይህም ዜጎች እና የንግድ ድርጅቶች በእነርሱ ላይ ተፈጻሚነት ያላቸውን ደንቦች እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል፡፡

- **የኤሌክትሮኒካዊ ክትትል፡-** ቴክኖሎጂ ደንቦችን መከበራቸውን ለመከታተል እንደ አውቶሜትድ ፍተሻ ወይም መረጃ ትንተና መጠቀም ይቻላል።

## 10. የጠቋሚዎች ጥበቃ

ጠቋሚዎች ህገወጥ እና ስነምግባር የጎደላቸው ተግባራትን በማጋለጥ ሙስናን በመዋጋት ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ነገር ግን፣ ጠቋሚ መሆን ብዙ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የግል ዋጋ ያስከፍላል፣ ይህም ከስራ ማጣት፣ ከማህበራዊ መገለል እና ሌላው ቀርቶ ለደህንነታቸው አስጊ ሊሆን ይችላል። ግለሰቦች ወደ ፊት እንዲመጡ ለማበረታታት ጠንካራ የህግ ከለላዎችን መስጠት አስፈላጊ ነው።

- **ቁልፍ የህግ ጥበቃዎች ለጠቋሚዎች**
  - ***ማንነትን መደበቅ እና ምስጢራዊነት፡-*** ጠቋሚዎች ማንነታቸውን ለህዝብ ይፋ እንዳይሆኑ በመጠበቅ ሙስናን በድብቅ ወይም በሚስጥር እንዲዘግቡ መፍቀድ ያስፈልጋል። ይህ የበቀል ወይም የትንኮሳ አደጋን ለመቀነስ ይረዳል።
  - **ከአጸፋ መከላከል፡-** ሕጎች በግልጽ መረጃ በሚናገሩ ሰዎች ላይ የበቀል እርምጃ እንዳይወሰድባቸው መከላከል አለባቸው። የበቀል እርምጃ የሚባሉት ለምሳሌ የቅጥር መቋረጥ፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግ፤ የደመወዝ ቅነሳ፤ አድልዎ፤ ትንኮሳ ይገኙበታል።
  - **ህጋዊ ውክልና፡** ጠቋሚዎች ህጋዊ ሂደቱን ለመምራት እና መብቶቻቸውን ለማስጠበቅ እንዲረዳቸው የህግ ውክልና ማግኘት አለባቸው።
  - **የፋይናንሺያል ማካካሻ፡-** በአንዳንድ ሁኔታዎች መረጃ ጠቋሚዎች የገንዘብ ማካካሻ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፣በተለይ የእነርሱ መገለጥ ለመንግስት ወይም ለድርጅት ከፍተኛ ቁጠባ ወይም ማገገሚያ የሚወስድ ከሆነ።
  - **ከሐሰት ውንጀላዎች ጥበቃ፡-** ከከንቱ ወይም ተንኮለኛ ውንጀላዎች ለመከላከል ሕጎች የይገባኛል ጥያቄያቸውን የሚደግፍ ምክንያታዊ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ነጋሪዎችን የሚጠይቁ ድንጋጌዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

## 11. መደበኛ ኦዲት እና ምርመራዎች

ኦዲት እና ቁጥጥር የንግድ እና የኢንቨስትመንት ሂደቶችን ታማኝነት እና ግልጽነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል በተለይም ከቀጣናዊ ትስስር። ሕገወጥ ድርጊቶችን በመለየት፣

ማጭበርበርን በመከላከል እና ደንቦችን፣ ኦዲቶችን እና ፍተሻዎችን ማክበርን በማስተዋወቅ ለንግድ ድርጅቶች እና ባለሀብቶች የበለጠ ደረጃ ያለው የመጫወቻ ሜዳ እንዲፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል።

**በንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ውስጥ የትኩረት ቁልፍ ቦታዎች**

- **ታሪፍ እና ኮታ ማክበር፡-** ታሪፍ እና ኮታ በትክክል መተግበሩን እና ለተወሰኑ አስመጪዎች ወይም ላኪዎች ምንም አይነት ቅድመ አያያዝ አለመኖሩን ኦዲት ማድረግ።
- **የንግድ ማመቻቸት ስምምነቶች፡-** ኦዲት ከጉምሩክ አሠራሮች፣ ከድንበር አስተዳደር፣ ከንፅህናና ከዕፅዋት ጥበቃ እርምጃዎች ጋር የተያያዙ የንግድ ማመቻቸት ስምምነቶችን መከበራቸውን መቆጣጠር።
- **የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፡-** ኦዲት በማድረግ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች አግባብነት ባላቸው ህጎችና መመሪያዎች እየተሰጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ። ይህም ሙስናን ለመከላከል እና የእነዚህ ማበረታቻዎች ጥቅማጥቅሞች በፍትሃዊነት እየተከፋፈሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል።
- **የቀጣናዊ የንግድ ስምምነቶች፡-** ኦዲት እንደ ነፃ የንግድ ስምምነቶች እና የጉምሩክ ማህበራት ያሉ የክልል የንግድ ስምምነቶችን መከበራቸውን ለመቆጣጠር ይረዳል። ይህም የእነዚህ ስምምነቶች ጥቅሞች እውን መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል።

**12. የሲቪል ማህበረሰብ ተሳትፎን ማጠናከር**

የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሂደቶች ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና መልካም አስተዳደርን በማስፈን የሲቪል ማህበረሰብ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። እነዚህን ሂደቶች በመከታተል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሚዲያዎች ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት ለመፍታት፣ የትስስር ጥቅሞች በፍትሃዊነት እየተከፋፈሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና መንግስታትን ለዜጎቻቸው ተጠያቂ ለማድረግ ይረዳሉ።

**የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች (መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) እና ሚዲያዎች ቁልፍ ሚናዎች:-**

- **ክትትልና ድጋፍ፡-** መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሚዲያዎች እንደ ሙስና፣ ኢ-ፍትሃዊ የንግድ ተግባራት፣ እና አሉታዊ የአካባቢ ወይም ማህበራዊ ተፅእኖዎች ያሉ ችግሮችን ለመለየት የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሂደቶችን መከታተል ይችላሉ። ከዚያም እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ማሻሻያዎችን እና የፖሊሲ ለውጦችን መደገፍ ይችላሉ።

- **የህዝብ ግንዛቤ፡-** *መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና መገናኛ ብዙኃን ስለ ንግድና ክልላዊ ውህደት ጥቅሞችና ተግዳሮቶች ግንዛቤ ማሳደግ ይችላሉ። ይህም ለእነዚህ ሂደቶች ድጋፍን ለማጎልበት እና የህዝቡን ድምጽ ለመስማት ይረዳል።*
- **ተሳትፎ፡-** *መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና መገናኛ ብዙኃን በንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሂደቶች የህዝብ ተሳትፎን ማመቻቸት ይችላሉ። ይህም የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት ለማረጋገጥ ይረዳል።*
- **ተጠያቂነት፡-** *መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሚዲያዎች በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ረገድ ለሚያደርጉት ድርጊት መንግሥትንና የንግድ ድርጅቶችን ተጠያቂ ማድረግ ይችላሉ። ይህም ሙስናን ለመግታት እና የውህደት ፋይዳው በፍትሃዊነት እየተከፋፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ ያስችላል።*
- **አማራጭ አመለካከቶች፡-** *መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች በንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ላይ አማራጭ አመለካከቶችን ሊሰጡ ይችላሉ፣ የበላይ የሆኑትን ትረካዎች በመቃወም እና የበለጠ አሳታፊ እና ፍትሃዊ አቀራረብን ማራመድ ይችላሉ።*

## 13. ለአመራሮች፣ ሰራተኞች እና ባለድርሻ አካለት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት

*ሥነ ምግባርን ለማስተዋወቅ፣ ሙስናን ለመከላከልና የንግድ ፖሊሲዎችን ውጤታማ ለማድረግ ለንግድና ጉምሩክ ባለሥልጣኖች አቅም ማሳደግ አስፈላጊ ነው። ለባለሥልጣናት አስፈላጊውን እውቀት፣ ክህሎት እና መሳሪያ በማቅረብ አቅምን ማሳደግ ለንግድ ስራ ግልፅ እና ተጠያቂነት ያለው አካባቢ ለመፍጠር ያስችላል።*

- **በአቅም ግንባታ ውስጥ የትኩረት ቁልፍ ቦታዎች: -**
  - **የሥነ ምግባር ደረጃዎች፡-** *ሥልጠና በሕዝብ አገልግሎት ውስጥ የሥነ-ምግባር ደረጃዎች ያለውን ጠቀሜታ እና ብልሹ ባህሪ ውስጥ መግባት የሚያስከትለውን መዘዝ ሊያጎላ ይገባል። ባለሥልጣናቱ የጥቅም ግጭት፣ ጉቦና ሌሎች ሥነ ምግባራዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን በመለየት እና ለማስወገድ መመሪያ ሊሰጣቸው ይገባል።*
  - **የፀረ-ሙስና ሕጎችና ደንቦች፡-** *አግባብነት ያላቸውን የጸረ-ሙስና ሕጎችና ደንቦችን ለንግድና ጉምሩክ ኃላፊዎች የሚመለከቱ ሥልጠናዎች ሊሸፍኑ ይገባል። ይህ ከጉቦ፣ ከህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር እና የጥቅም ግጭት ጋር የተያያዙ ህጎችን ይጨምራል።*

- **የምርመራ እና የማስፈጸሚያ ቴክኒኮች፡-** ባለስልጣኖች በምርመራ እና የማስፈጸሚያ ቴክኒኮች፣ ማስረጃዎችን እንዴት መሰብሰብ፣ ቃለ መጠይቅ ማድረግ እና የክስ መዝገቦችን ማዘጋጀትን ጨምሮ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል።
- **የአደጋ ምዘና እና መከላከል፡-** ሥልጠና ባለሥልጣናት በንግድና ጉምሩክ ሂደቶች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ተጋላጭነቶችን ለመለየት እንዲረዳቸው የአደጋ ግምገማ ቴክኒኮችን መሸፈን አለበት። ይህም የመከላከያ እርምጃዎችን በመተግበር ሙስናን ለመከላከል ይረዳል።
- **ግልጽነትና ተጠያቂነት፡-** ስልጠና ግልጽነትና ተጠያቂነት በንግድና ጉምሩክ ሥራዎች ላይ ያለውን ጠቀሜታ አፅንዖት መስጠት አለበት። ባለሥልጣናቱ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማሻሻል ቴክኖሎጂን እንዴት እንደሚጠቀሙ ለምሳሌ በኤሌክትሮኒክስ የጉምሩክ መግለጫዎችና በኦንላይን የክፍያ ሥርዓቶች ማስተማር አለባቸው።
- **አለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች፡-** ስልጠና አለም አቀፍ የንግድና የጉምሩክ መልካም ተሞክሮዎችን ማካተት አለበት። ይህ ባለሥልጣኖች በመስክ ውስጥ ያሉ የቅርብ ጊዜ አዝማሚያዎችን እና እድገቶችን እንዲያውቁ ለማድረግ ይረዳል።

## 14. የህግ ማዕቀፎችን ማጠናከር

በንግዱ ዘርፍ ሙስናን ለመዋጋት ጠንካራ የህግ ማዕቀፎች ወሳኝ ናቸው። ጠንከር ያለ የፀረ-ሙስና ህግጋትን እና ቅጣቶችን በማስፈፀም መንግስታት ብልሹ ባህሪን መከላከል፣ግልፅነትን ማስተዋወቅ እና ለንግድ ስራ ምቹ የመጫወቻ ሜዳ መፍጠር ይችላሉ።

- **የጠንካራ የህግ ማዕቀፍ ቁልፍ አካላት /ይዘቶች/:-**
  - **ሁሉን አቀፍ የፀረ-ሙስና ሕጎች፡-** መንግስታት የሙስና መከላከል ህጎችን በማውጣት ጉቦ፣ ምዝበራ እና ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ጨምሮ ዘርፈ ብዙ ወንጀሎችን የሚሸፍኑ ህጎችን ማውጣት አለባቸው። እነዚህ ህጎች ግልጽ፣ የማያሻማ እና ተፈጻሚ መሆን አለባቸው።
  - **ጥብቅ ቅጣቶች፡-** የሙስና ቅጣቶች ወንጀለኞችን ለመከላከል ከባድ መሆን አለበት። ይህም መቀጮ፣ እስራት እና ሌሎች የቅጣት ዓይነቶችን ይጨምራል።
  - **የንብረት ማስመለስ፡-** በሙስና የተገኙ ንብረቶችን ለማስመለስ መንግስታት ውጤታማ ዘዴዎች ሊኖራቸው ይገባል። ይህም ከህገ ወጥ ተግባራት ጋር ተያይዞ የሚኖረውን የገንዘብ ሽልማት በመቀነስ ሙስናን ለመከላከል ይረዳል።

- **ለጠቋሚዎች ጥበቃ፡-** ሙስናን የሚዘግቡ ጠቋሚዎች ከበቀል ሊጠበቁ እና እንዲቀርቡ ማበረታቻ ሊደረግላቸው ይገባል። ይህ ግለሰቦች ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን ሪፖርት እንዲያደርጉ ለማበረታታት ይረዳል።
- **ግልጽነትና ተጠያቂነት፡-** ሕጎች የመንግሥት ባለሥልጣናት የገንዘብ ጥቅማቸውንና ንብረታቸውን እንዲገልጹ ማድረግ አለባቸው። ይህም የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል እና ግልጽነትን ለማስፋፋት ይረዳል።

## 15. ክልላዊ (ቀጣናዊ) ትብብር

በተለይም ድንበር ዘለል ንግድና ኢንቨስትመንት ጉልህ በሆነባቸው ክልሎች ሙስናን በብቃት ለመዋጋት ክልላዊ/ቀጣናዊ ትብብር ወሳኝ ነው። የክልል አካላት በጋራ በመስራት የፀረ-ሙስና ደንቦችን ማሳደግ፣ ጥረቶችን ማስተባበር እና ምርጥ ተሞክሮዎችን ማካፈል ይችላሉ።

➢ **የክልል/ቀጣናዊ/አካላት ቁልፍ ሚናዎች:-**

የክልል/ ቀጣናዊ/ አካላት የፀረ-ሙስና ደንቦችን በማዘጋጀት እና በድንበር ላይ በማስተዋወቅ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ይህ ክልላዊ ስምምነቶችን፣ የሥነ ምግባር ደንቦችን እና አገሮች ሊከተሏቸው የሚችሏቸውን ምርጥ ልምዶችን ማዳበርን ሊያካትት ይችላል።

የክልል/ቀጣናዊ/ አካላት ሙስናን ለመዋጋት አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን፣ ህጎችን እና የሰው ሀይልን በማፍራት ለአባል ሀገራት የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ።

የክልል/ቀጣናዊ/ አካላት የፀረ-ሙስና ጥረቶችን በአባል ሀገራቱ መካከል ማስተባበር፣ በፖሊሲዎች እና አሰራሮች ላይ ወጥነት ያለው እና ወጥነት እንዲኖረው ማድረግ ይችላሉ።

የክልል/ቀጣናዊ/ አካላት ከሙስና ጋር የተያያዙ መረጃዎችን እና የመረጃ ልውውጥን ማመቻቸት ይችላሉ። ይህም ድንበር ተሻጋሪ የሙስና መረቦችን ለመለየት እና ለመፍታት ይረዳል።

ከሙስናና ንግድ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችን ለመፍታት የክልል/ቀጣናዊ/ አካላት የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ማዘጋጀት ይችላሉ። ይህ ግጭቶችን ለመከላከል እና ትብብርን ለማበረታታት ይረዳል።

❖ ፀረ-ሙስናን የሚያራምዱ የክልል /ቀጣናዊ/ አካላት ምሳሌዎች: -

- **የአፍሪካ ህብረት፡** የአፍሪካ ህብረት ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚያስችል ስምምነት በአፍሪካ የፀረ-ሙስና ህጎችን እና ተቋማትን ደረጃዎችን አስቀምጧል። የአፍሪካ ኅብረት ለአባል አገሮች የቴክኒክ ድጋፍ የሚያደርግ የፀረ ሙስና ክፍል አለው።
- **የአውሮፓ ሕብረት፡** የአውሮፓ ኅብረት በርካታ የፀረ-ሙስና መሣሪያዎች አሉት፣የጋራ አስተዳደራዊ ድጋፍ በታክስ ጉዳዮች ኮንቬንሽን እና በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ድጋፍ ስምምነትን ጨምሮ። የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ትብብርን የሚያበረታቱ የፀረ-ሙስና አስተባባሪዎች መረብ አለው።
- **የኤስያን ክልላዊ ፎረም** (ASEAN Regional Forum፡ የ ASEAN ክልላዊ ፎረም በደቡብ ምስራቅ እስያ በሚገኙ ሀገራት መካከል የውይይት እና የትብብር መድረክ ነው። በደቡብ ቻይና ባህር ውስጥ የኃላፊነት ባህሪን የሚመለከት የስነ ምግባር ደንብ አጽድቋል፣ ይህም ግልጽነት እና ፀረ-ሙስናን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ያካትታል።

## 16. የመንግስት-የግል ዘርፍ ሽርክናዎች (Public-Private Partnerships) መፍጠር

የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ሽርክና (PPPs) ሥነ ምግባራዊ የንግድ ሥራዎችን ለማስተዋወቅና ሙስናን ለመዋጋት ኃይለኛ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። የንግድ ድርጅቶች የታማኝነት ስምምነቶችን እና የሥነ ምግባር ደንቦችን እንዲከተሉ በማበረታታት፣ መንግስታት ለንግድ እና ኢንቨስትመንት የበለጠ ግልፅ እና ተጠያቂነት ያለው አካባቢ መፍጠር ይችላሉ።

### ➢ የታማኝነት ስምምነቶች እና የስነምግባር ህጎች (Integrity Pacts and Codes of Conduct)

የታማኝነት ስምምነቶች እና የስነምግባር ደንቦች በመንግስታት እና የግሉ ዘርፍ መካከል የሚደረጉ የፍቃደኝነት ስምምነቶች የስነ-ምግባር መስፈርቶችን የሚያወጡ ናቸው። እነዚህ ሰነዶች ግልጽነት፣ የጥቅም ግጭት፣ ጉቦ እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ድንጋጌዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

የታማኝነት ስምምነት እና የስነምግባር ደንቦች በርካታ ጥቅሞች አሏቸው፣ ከእነዚህም መካከል፡-

- **የሙስና አደጋን መቀነስ፡-** ለሥነ ምግባር ግልጽ የሆኑ መመዘኛዎችን በማውጣት እነዚህ ስምምነቶች በንግድ ሥራ ላይ የሚደርሰውን የሙስና አደጋ ለመቀነስ ይረዳሉ።

- **የሕዝብን ገጽታ ማሻሻል፡** የንጹህነት ስምምነቶችን እና የሥነ ምግባር ደንቦችን ያከበሩ የንግድ ድርጅቶች ህዝባዊ ገጽታቸውን እና ስማቸውን ሊያሻሽሉ ይችላሉ።
- **የገበያ መዳረሻን ማመቻቸት፡-** አንዳንድ መንግስታት ለመንግስት ኮንትራቶች ወይም ሌሎች የንግድ እድሎች ብቁ ለመሆን የንግድ ድርጅቶች የታማኝነት ውሎችን ወይም የስነምግባር ደንቦችን እንዲያወጡ ሊጠይቁ ይችላሉ።

## 17. ተቋማዊ የአፈፃፀም ፍተሻ ማድረግ እና ማሻሻያ ማካሄድ

ሙስናን ለመዋጋትና በንግዱ ዘርፍ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከንግድ ጋር የተያያዙ ተቋማትን ማጠናከር ወሳኝ ነው። እነዚህ ተቋማት በገንዘብ የተደገፉ፣ ገለልተኛ እና ግልጽነት ያላቸው መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ መንግስታት ለንግድና ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይችላሉ።

➢ **የተቋማዊ ማሻሻያ ቁልፍ ቦታዎች:-**

- **ነፃነት፡-** ከንግድ ጋር የተያያዙ ተቋማት ከፖለቲካዊ ጣልቃገብነት ነፃ ሆነው ተግባራቸውን ያለአንዳች ተፅዕኖ የመወጣት ሥልጣን ሊኖራቸው ይገባል። ይህ ግልጽ በሆነ ስልጣን፣ በቂ የገንዘብ ድጋፍ እና ከፖለቲካዊ ደጋፊነት ጥበቃዎች ሊገኝ ይችላል።
- **ግልጽነት፡** ተቋማቱ በእንቅስቃሴያቸው፣በውሳኔዎቻቸው እና በፋይናንሺያል ሂሳባቸው ላይ መረጃዎችን በማተም በሚሰሩበት ጊዜ ግልፅ መሆን አለባቸው። ይህም መተማመንን ለመፍጠር እና ሙስናን ለመከላከል ይረዳል።
- **ተጠያቂነት፡-** ተቋማት ተጠሪነታቸው ለህዝብ እና ለክትትል አሰራር ተገዢ መሆን አለበት። ይህ ኦዲት ማድረግን፣ ምርመራዎችን እና የፓርላማ ምርመራን ሊያካትት ይችላል።
- **የአቅም ግንባታ፡-** ተቋማት ተግባራቸውን በብቃት ለመወጣት አስፈላጊው አቅም ሊኖራቸው ይገባል። ይህ በስልጠና፣ በቴክኖሎጂ እና በመሠረተ ልማት ላይ ኢንቨስት ማድረግን ሊያካትት ይችላል።
- **ትብብር፡** ተቋማቱ ከሌሎች የሚመለከታቸው ኤጀንሲዎች ከአገር ውስጥም ሆነ ከአለም አቀፍ ጋር በመተባበር መረጃን ለመለዋወጥ፣ ጥረቶችን ለማስተባበር እና መልካም ተሞክሮዎችን ማሳደግ አለባቸው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በምዕራፍ 3 በመጀመሪያው ንዑስ ክፍል ሙስና በንግዱ ዘርፍ የሚያስከትለውን ተፅእኖ ወይም ጉዳት የቀረበ ሲሆን፤ በሁለተኛው ንዑስ ክፍል ደግሞ የሙስና መከላከያ ስልቶች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ ሙስና ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ህጋዊና ተቋማዊ ተፅእኖ እንደሚያደርስ በስፋትና በጥልቀጥ ተብራርቷዋል፡፡ ስለሆነም የሙስና ጉዳት በተቋማት ላይ ከፍተኛ እና ዘርፈ-ብዙ መሆኑን በዚህ ምእራፍ መረዳት ይቻላል፡፡

ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም በአንድ ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና የብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ስልት የለም፡፡ ይሁንና እንደተቋሙ ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም በየጊዜው የሚለዋወጠውን የሙስና ስትራቴጂ ግምት ውስጥ ያስገባ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘጠኝ ስትራቴጂዎች ተመላክተዋል፡፡ ይሁንና የመከላከያ ስልቶቹ ስምንት ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በማምጣት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

➢ ***ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡***

1. ሙስና በምትሰሩበት ተቋም የሚያስከትለውን የጉዳት አይነቶች ዘርዝሩ፡፡
2. በተራ ቁጥር 1 የዘረዘራችኋቸው የሙስና የጉዳት አይነቶች በንግዱ ዘርፍ ምን ያህል ጉዳት እያደረሱ መሆኑን ተወያዩ፡፡
3. ሙስና በንግዱ ዘርፍ የሚያደርሰውን ጉዳት ምንጮች ምንምን ናቸው?
4. በዚህ ስልጠና ከተካተቱት የሙስና የመከላከያ ስልቶች መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ የተደረጉት የትኖቹ ናቸው? የተገኘውስ ለውጥ ምንድን ነው?

5. “ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀል”ን ለመከላከል የሃብት እና ጥቅም ምዝገባ ከንግዱ ዘርፍ ጋር ትስስር ያላቸው አካላት ማድረጋቸው ሙስናን እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ።
6. በዚህ ስልጠና ውስጥ ከተመለከታችሁት የመከላከያ ስትራቴጂወቸወ መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ ያልተደረጉት የትኖቹ ናቸው? ላለመፈፃማቸው እንደ ምክኒያት የሚጠቀሱት ምንድናቸው?
7. ከምትሰሩበት የስራ አካባቢ አንጻር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በዝርዝር ለተሳታፊዎች አስረዱ።
8. በንግዱ ዘርፍ ኢ-ገቨርናንስን/ዲጂታል መንግስታዊ አስተዳደር/ መጠቀም ያለውን ጥቅም ተወያይ።
9. በጠቋሚዎች ጥበቃ ውስጥ ስላሉት ተግዳሮቶች እና ታሳቢዎች ተወያዩ።
10. በዚህ ስልጠና ከተካተቱት በተጨማሪ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ዘርዝሩና ለተሳታፊዎች አስረዱ።
11. እነደ ሀገርም ሆነ በተቋም ደረጃ የፀረ-ሙስና ሕጎችን ማስከበር ፈታኝ ሊሆን ይችላል ብለው ያስባሉ? ለምን?

- ***በሚቀጥለው ገፅ የተፃፉትን ሁለት ኬዞች በማንበብ ከቡድን አባላት ጋር በመወያየት ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ።***

***ኬዝ አራት፡***

*የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መ/ቤት የመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን የመቆጣጠር፣ ሥርዓቶች መዘርጋትና ተግባራዊ የማድረግ ሀላፊነት የተሰጠው መሆኑ እሙን ነው። ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን ለማቀላጠፍ የሚያስችሉ የህግ ማእቀፎች፡ የንግድ ፖሊሲዎች እንዲፀድቁ ባለማድረጉ እና ባለመተግበሩ፣ የንግዱ ዘርፉ በህግ፣ በግልፅነት እና ወጥ በሆነ ምልኩ እንዳይመራ እና ጤናማ የግብይትና የስርጭት ሥርአት እንዳይኖር አድርጓል።*

*እንዲሁም የፍራንኮቫሉታ አስመጪዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ ቢፈቀድላቸውም የስርጭትና ግብይት ስርዓት ባለመዘርጋቱ በፍራንኮቫሉታ ሊሸፈን የታሰበው የመሰረታዊ ሸቀጥ ፍላጎት እንዳይሸፈን በማድረጉ የኑሮ ውድነቱ እንዳይቀንስ እና ገበያው እንዳይረጋጋ የበኩሉን ድርሻ አበርክቶል። በተጨማሪም የቁጥጥር እና ትስስር ስርዓት እንዳይኖር በመደረጉ ተጠያቂነትና ፍትሃዊነት የሰፈነበት የግብይትና የስርጭት ሰንሰለት እንዳይኖር እና ምርቶቹ ለሁሉም አከባቢዎች ተደራሽ እንዳይሆኑ አድርጓል።*

*ኬዝ አምስት፥*

*በ2015 የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ለቦቴ የካሊብሬሽን እና የጥራት ቁጥጥርና ዲፖ የሚገኘውን የነዳጅ ስርጭት እንዲቆጣጠሩ ሁለት የጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎችን መድቦ ስራው እንዲከናውን ወደ ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን አዴሌ ከተማ ልኳቸው ነበር። የከተማው ፖሊስ ሁለቱን ባለሙያዎች ከሾፌራቸው ጋር በቁጥጥር ስር በማዋል በሙስና ወንጀል እንደከሰሳቸውና በዋስ ከመለቀቃቸው በፊት ለስድስት ወራት ያህል መታሰራቸውን የመረጃ ምንጮች ያሳያሉ። በዋስ ከእስር ቢፈቱም ሚኒስቴሩ ደመወዛቸውን በማገድ የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለሚመለከተው አካል መርቷዋል፣ ምርመራው አሁንም እንደቀጠለ ነው። ይህ ክስተት በኢትዮጵያ የንግድ ቁጥጥር ስርዓት በተለይም በክልላዊ ስራዎች ላይ ስላለው ታማኝነት እና ተጠያቂነት ያለውን ሰፊ ስጋት አጉልቶ ያሳያል። (ምንጭ፡ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር)*

*ጥያቄዎች:*

- ***በክልል ንግድ ቁጥጥር ላይ ሙስናን ለመከላከል ምን አይነት ዕርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል;***
- ***ንግድ ሚኒስቴር በሥነ ምግባር ጉድለት ለተከሰሱ ኃላፊዎች በዲሲፕሊን ሂደት ውስጥ ፍትሃዊ እና ተጠያቂነትን እንዴት ማረጋገጥ ይችላል?***

*ኬዝ ስድስት፥*

*በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 02 ሃያት ጣፎ ሽርክና ህብረት ስራ ማህበር በ14/03/2015 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ከስኳር ኢንደስትሪ ግሩብ ከገዙት ስኳር ውስጥ 113 (አንድ መቶ አስራ ሶስት) ኩንታል የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት እና የተበላሸ መሆኑና የሚመለከተው አካል ችግሩን እንዲፈታ አመልክተው ነበረ። የከተማ አስተዳደሩም ይህን ጉዳይ ያረጋገጠ በመሆኑና የጥራት ኮሚቴ ሪፖርትም አያየዞ ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ልኮል። ነገር ግን የሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ 1263/2014 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሀገር ውስጥ ንግድና ሸማቼች ጥበቃ እና የጥራት ማረጋገጥ መሪ ስራ አስፈፃሚ ባለሙያዎችን በ27/6/2015 በተባለው ቦታ ስኳሩን ፈትሸው የተባለውን ችግር እንዲጣራ መላኩንና የተባልው ችግር እንደሌለ ማስረዳታቸውን የንግድና ቀጠናቂ ትስስር ሚኒስቴር መ/ቤት በጥር 15/2015 በቁጥር ቸነ/2315/10-6 በስኳር እንደስትሪ ግሩፕ ላይ የቀረበ የጥራት ቅሬታ ውድቅ መሆኑን በፃፈው ደብዳቤ አሳውቋል።*

*በተመሳሳይ በደቡብ ክልል በዲላ እና በጋሞ የሸማቾች ማህበራት ከሱኳር ኮርፖሬሽን ከገዙት 1363 ኩንታል ስኳር ውስጥ 90 በመቶ የተበላሸ መሆኑን አስረድተው እንዲቀየር በደብዳቤ ቢጠይቁም*

## የሞጁሉ ማጠቃለያ

ይህ የስልጠና ሞጁል የተዘጋጅው የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና በስሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ አመራሮች እና ሰራተኞች ስለ ሙስና ወንጀል ምንነት፤ የሙስና ዓይነቶች፤ ተቋሙ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት፤ ሙስና የሚያስከትለው ጉዳትና የመከላከያ ስልቶች በተመለከተ ግንዘቤያቸውን እንዲያደብሩ እና የፌደራል ስነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስናን በሀገራችን ለመከላከል በሚያደርገው ጥረት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ነው፡ ፡

ከላይ የተጠቀሰውን ዓላማ ለማሳካት ይህ ሞጁል በሶስት ምዕራፎች ተከፋፍሉ ከሙስና ጋር ተዛማጅ የሆኑ ርዕሶች ቀርቧል፡፡ በእያንዳዱ ምዕራፍ የማነቃቂያ እና መወያያ ጥያቄዎች እንዲሁም ኬዞች የቀረቡ ሲሆን ሰልጣኞች በቡድን በመያየት ለጥያቄዎቹ ምልሽ እንዲሰጡ ይጠበቃል፡፡ በመጨረሻም ሰልጣኞች ከስልጠናው በኃላ ያላቸውን ግንዘቤ ደረጃ ለመገምገም ቼክ ሊስት የተዘጋጀ ሲሆን በዚሁ መሰረት ራሳቸውን ይገመግማሉ፡፡ ስልጠናው የ ሁለት ቀናት ወይም 12 ስዓታት የሚወሰውድ ሲሆን የስልጠናው ወቅትም በኮሚሽኑ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## የሰልጣኞች ብቃት መገምገሚያ ጥያቄዎች

*ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የተካተቱትን የብቃት መገምገሚያ ጥያቄዎች በተቀመጡት አማራጮች መሠረት የ (X) ምልክት በማድረግ ምላሽ ስጡ፡፡*

| ተ.ቁ | የብቃት መለኪያዎቹ ዝርዝር | አማራጮች | |
|---|---|---|---|
| | | አዎ | አይደለም |
| 1 | የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚንስቴር ተግባርና ሃላፊነትን ጠንቅቄ አውቃለሁ፡፡ | | |
| 2 | የሙስናን ጽንሰ ሀሳብ በሚገባ ተረድቻልሁ፡፡ | | |
| 3 | ሙስና ወንጀል መሆኑን በመገንዘብ ለሌሎች ማስረዳት እችላለሁ፡፡ | | |
| 4 | የሙስናን መገለጫዎች በሚገባ ማስረዳት እችላለሁ፡፡ | | |
| 5 | በኢትዩጵያ ንግድ ሥርዓት ውስጥ የሚከሰቱትን የሙስና ኣይነቶች መግለጽ እችላሁ | | |
| 6 | የሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭንት ማለት ምን እንደሆነ በሚገባ ማብራራት እችላለሁ፡፡ | | |
| 7 | የኢትዮጵያን ንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት በሚገባ መለየት እችላለሁ፡፡ | | |
| 8 | የኢትዮጵያን ንግድ ዘርፉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች የተጋላጭነት ምክንያቶች ተረድቸ መዘርዘር እችላለሁ፡፡ | | |
| 9 | የኢትዮጵያን ንግድ ዘርፉ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለዉን አንድምታ መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | |
| 10 | የንግዱ ዘርፉ  ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያለዉን ግንኙነት መተንተን እችላለሁ፡፡ | | |
| 11 | ሃላፊነትና ተጠያቂነት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር የሚኖራቸዉን ቁርኝት በመገንዘብ ሚናየን በአግባቡ መወጣት እችላለሁ፡፡ | | |
| 12 | ሥነ-ምግባር እና እሰቶቸ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉን ግንኙነት በመገንዘብ ጥሩ ሥነ-ምግባርና መልካም እሰቶችን በተላበሰ መልኩ ስራዎችን መፈጸም እችላለሁ፡፡ | | |
| 13 | በምሰራበት መስሪያ ቤት የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ነባራዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል መተንተን እችላለሁ፡፡ | | |
| 14 | በመስኩ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት የጉዳት መጠን መለየት እችላለሁ፡፡ | | |
| 15 | የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መንሰራፋት በትዉልድና በአገር ግንባታ ስራዎች ላይ የሚኖረዉን አሉታዊ ተጽዕኖ መተንተን እችላለሁ፡፡ | | |
| 16 | ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሏቸዉን ጉዳቶች በሚገባ በመረዳት ሌሎች የስራ ባለደረቦች ግንዛቤ እንዲያገኙ የበኩሌን በጎ አስተዋጽኦ ማድረግ እችላለዉ፡፡ | | |
| 16 | የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችን ምንነትና ተግባራዊነትን ለይቼ አውቃለሁ ፡፡ | | |
| 17 | በመስኩ የተለዩትን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችን በመተግበር ግንባር-ቀደም ተምሳሌት በመሆን ስራዬን አከናዉናለሁ፡፡ | | |

## ማጣቀሻ ፅሁፎች


- በታሪክ አዱኛ FBC (Fana Broadcasting Corporate S.C.)'s Post October 16, 2024
- Addis Standard, 2024: https://addisstandard.com/news-ethiopia-charges-four.../
- Proclamation No. 1263/2021 Definition of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation, January, 2022.
- የንግድና ቀጠናዊ ትስስር የዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት, 2015


.

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION
ስልክ;- +251115-52-77-85/+251115-53-69-01
ፖሳቁ P.O.Box :- 34798/99
ኢ-ሜይል:- E-mail FeaccEthiopia2013@et
ፌስቡክ/www.facebook.com/feaccOfficial
ድረ-ገጽ/ www.feacc.gov.et